**የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 6 (2) (ሐ) እና አንቀጽ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልጽ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የሚደነግግ በመሆኑና ይህን ሪፖርት ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እየገለፅኩ መ/ቤታችን በ2009/2010 በጀት ዓመት ያከናወናቸውን የክዋኔ ኦዲት አጭር ሪፖርት ለተከበረው የም/ቤት ጉባዔተኛ እንደሚከተለው በንባብ አቀርባለሁ፡፡
2. *በዚህ አጭር ሪፖርት የቀረበው መ/ቤታችን በ2009/2010 የኦዲት ዘመን ኦዲት አድርጎ ያጠናቀቃቸውን የ6 መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ይሆናል፤*
3. የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ያቀዷቸውን ስራዎች በተመደበላቸው ሃብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በቅልጥፍና እና በውጤታማነት በመፈጸም የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ የተከናወነ ኦዲት ነው፤

በዘገባ ሪፖርቱ ከተዘጋጁት የክዋኔ ኦዲቶች መካከል 1ኛ.የጎንደር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠናና የስራ እድል ፈጠራ ትስስርን በተመለከተ፤ 2ኛ.የአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ በደን ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ፣ 3ኛ.በእንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ የእንስሳት ጤና አገልግሎት መድሃኒት አጠቃቀምና ስርጭት፤ 4ኛ.በመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የሁሉን አቀፍ ገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም (URRAP) አፈጻጸምና ውጤታማነት በተመለከተ፣5ኛ.በጤና ጥበቃ ቢሮ የህክምና መሳሪዎች፣ መድሃኒቶች፣ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አቅርቦት፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ በተመለከተ እና 6ኛ.የአደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወኑ የኦዲት ውጤቶችን ይሆናል፡፡

የእያንዳንዱን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ሪፖርት ዝርዝር ውጤት የያዘ አስቀድሞ ለየመ/ቤቶቹና ለተቆጣጣሪ አካላት የማሻሻያ አስተያየት ያካተተ የኦዲት ሪፖርት እንዲደርሳቸው አድርገናል፡፡ ሪፖርቱ ከተላከላቸው 6 መ/ቤቶች ውስጥ 4ቱ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ የመልስ መስጫ ጊዜያቸው ገና በመሆኑ እየተጠበቀ ነው፡፡ በዚህ አጭር ሪፖርት ከግኝቶች ጉልህነትና ከጊዜ አንጻር ስፋቱን ለመመጠን ሲባል ለተከበረው ም/ቤት ለንባብ የቀረበው በተመረጡ ውስን ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ በመሆኑ ዝርዝሩን ለማየት ሙሉ ሪፖርቱን ማንበብ ይጠይቃል፡፡

4. ለክዋኔ ኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዘርፎቹ እንዲመሩባቸው መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በህግ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት፣ የየመ/ቤቶች የስራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ከየመ/ቤቶቹ ደንበኞች/ ተገልጋዮች ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ስራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የኦዲት ስራውም ዓለም አቀፍ እና አገራዊ የክዋኔ ኦዲት አሰራር መርሆችና ስታንዳርዶችን ተከትሎ የተከናወነና ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ግኝቶች በናሙና በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ብቻ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባ እያስገነዘብኩ ከዚህ በመነሳት ዋና ዋና ግኝቶችን በአጭሩ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

## I. የጎንደር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠናና የስራ እድል ፈጠራ ትስስርን በተመለከተ፤

**በኮሌጁ □ስ□ በዉጭ ምንዛሬ ተገዝተዉና ለተግባር ስልጠና ገብተው ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሳሪያዎችን በተመለከተ**

5. በኮሌጁ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተገዝተዉ ለተግባር ስልጠና የገቡ መሳሪያዎች ያለ አገልግሎት ሊቀመጡ አይገባም፡፡ ይልቁንም በየደረጃዉ የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡ ይሁን እንጅ በኦዲት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተዉለዋል፡-
6. በ5 የትምህርት ክፍሎች ያለ አገልግሎት የተቀመጡ የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች መገኘታቸው ለአብነት፡-

6.1 በማኑፋክቸሪንግ ትምህርት ክፍል ብር 1,716,417.92 ግምት ያላቸዉ የተለያዩ ማሽኖች *(ዌልዲንግ ማሽን፣ ሬዚስታንስ ዌልዲንግ ማሽን፣ሂት ትሪትመንት ፈርኔስ፣ ድሪል ማሽን ፖርቴብል፣ ቸተኦፍ ማሽን፣ ስሊፕ ሮሊንግ ማሽን ማኑዋል፣ፋላንጊንግ ኤንድ ቤንዲንግ ማሽን እና ሀይድሮሊክ ፓይፕ ቤንደር)* እና የተገዙ የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች ከመቸ ጀምሮ እንደገቡ ጊዜው በማይታወቅበት ሁኔታ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን፤

6.2 ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በማሽን ዲፓርትመንት በብር 867,290.42 ተገዝቶ የገባ ሲኤንሲ ሚሊንግ ማሽን ከ3 አመት በላይ ሰልጣኞች ሳይጠቀሙበት ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፤

6.3 በእንጨት ስራ ትምህርት ክፍል ብር 634,368.57 ግምት ያላቸው (ማለትም ሰርኩላር ሳዉ፣ ቲክነስ ፒላነር፣ ባንድ ሳዉ ማሽን) ከመቸ ጀምሮ እንደገቡ ጊዜዉ የማይታወቅና ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆኑ እንዲሁም፤

6.4 ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ሰርፌስ ግራይንደር ማሽን በብር 610,872.46 ተገዝቶ ሰልጣኞች ሳይጠቀሙበት ከ10 አመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፤

6.5 ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ማሽን ዲፓርትመንት በድምሩ ብር 345,692.64 ዋጋ ያላቸው 2 ሴንተር ሌዝ ማሽን፤በአዲስነታቸው ከተተከሉ በኋላ ችግራቸው ሳይታወቅ ከ4 አመት በላይ ሰልጣኞች ሳይጠቀሙባቸው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

6.6 በቴክስታይል ጋርመንት ትምህርት ክፍል ብር 139,200.30 ግምት ያላቸዉ ማሽኖች *(ማለትም ኦቨር ሎክ ሲዊንግ ማሽን/ከ2009 ዓ/ም፣ በተን ሆል ሜኪንግ ሲዊንግ ማሽን* ) ከ2005 ዓ/ም እና ባር ታክ ሲዊንግ ማሽን ከመቸ ጀምሮ እንደተቀመጠ ጊዜዉ ያልታወቀ ያለ አገልግሎት የሚገኙ መሆናቸው፤

6.7 በአውቶሞቲቭ ትምህርት ክፍል ብር 56,272.87 ግምት ያላቸዉ የተለያዩ ማሽኖች *(ማለትም ኤር ኮምፕረሰር /ከ2002 ዓ/ም፣ ክሬን/ከ1990 ዓ/ም፣ፖርቴብል ድሪል)* ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ፣ኢንጀክተር ቴስተር የተባለ ማሽን ከ2003 ዓ/ም እና ክሪክ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆኑ፤

6.8 በሆቴልና ቱሪዝም ትምህርት ክፍል ብር 16,326.43 ያለው አይስክሬም ማሽን ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ፤

6.9 ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ብዛታቸዉ 2 የሆኑ ሲሊንደሪካል ግራይንዲንግ ማሽን እንደተተከሉ ሰልጣኞች ሳይጠቀሙበት ያለአገልግሎት ከ3 አመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፤

6.10 ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ዩኒቨርሳል ሚሊንግ ማሽን ሰልጣኞች ሳይጠቀሙበት ያለአገልግሎት ከ9 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤

6.11 ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ብዛት ሁለት ቤንች ድሪሊንግ ማሽኖች ከ7 ዓመት በላይ፤ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ብዛት 2 ስፒድ ሌዝ ማሽኖች ከ6 አመት በላይ እና ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ከተር ኤንድ ቱል ግራይንደር ማሽን ከ8 ዓመት በላይ ሰልጣኞች ሳይጠቀሙባቸው ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

7. ከኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በ2005 ዓ.ም ብዛት 4 የሽመና ማሽኖች ግዥ ተፈፅሞ አገልግሎት ሳይሰጡ ከ4 ዓመት በላይ በኮሌጁ የተቀመጡ መሆኑ፤

8. በ11/07/2006 ዓ/ም በጎንደር ከተማ በአዘዞ አየር ማረፊያ ክፍለ ከተማ ለሰንሻይን የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማህበር 10 የቆዳ ማሰልጠኛ ማሽኖች በትውስት መሰጠታቸውና እስከ ኦዲቱ ማጠናቀቂያ ከ5 ዓመት በላይ ባለመመለሳቸዉ በኮሌጁ የማሰልጠኛ ማሽን እጥረት የገጠመ መሆኑ በሰነድ ማስረጃ እና በአካል ምልከታ መረጋገጡ የሚሉት በዚህ ርዕስ ስር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይህም ሃብት የፈሰሰባቸው ማሽኖች ለታለመላቸው ዓላማ ባለመዋላቸው ተማሪዎች ብቁ ሆነው እንዳይመረቁ ከማድረጉ በተጨማሪ በተግባር ስልጠና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደራቸውም በላይ ተጨማሪ ሃብት ከማስገኘት ይልቅ ለሃብት ብክነትና ያለጥቅም ማርጀት የተጋለጡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

**በኮሌጁ በየአመቱ ተመርቀዉ የሚወጡ ሰልጣኞች የስራ ዕድል ፈጠራ ትስስርን፤ የስልጠናና ድጋፍን በተመለከተ፤**

9. በኮሌጁ በየአመቱ ተመርቀዉ የሚወጡ ሰልጣኞች ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር በሰለጠኑበት ሙያ ስራ የመያዝ እድልና ቀጣይነት ያለዉ ስልጠና በመስጠት 95% ስራ የመያዝና ቀጣይ የስልጠና እድል ሊፈጠርላቸዉ ይገባል፡፡ ይሁን እንጅ በኦዲት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተዉለዋል፡-

10. በ2006 በጀት ዓመት 18,061 ሰልጣኞች በአጫጭር ሥልጠና በማስልጠን የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ 4,300 /23.81%/ ሰልጣኞች ብቻ ሰልጥነው ከእነዚህ ውስጥ 3,082 /71.67%/ የሥራ ዕድል የተፈጥላቸዉ ሲሆን ከእቅዱ ደግሞ 17.06% ብቻ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ መሆኑ፤

10.1 በኮሌጁ የሥራ እድል መፍጠሪያ ሀብቶች ማለትም ለንግድ ስራ እቅድ ዝግጅት መሰረት የሚሆኑትን የመለየት ስራ የማይሰራ ሆኖ መገኘቱ፤

10.2 የሀብት መፍጠሪያ ፀጋዎችን አጠቃቀምና የቆይታ ጊዜ መወሰኛ የአሰራር መመሪያ አለመኖር፤

10.3 ከጎንደር ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዝ መምሪያ ደግሞ ተለይቶ የተደራጀ መረጃ ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፤

11. በ2007 በጀት አመት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአበዳሪ ተቋሙ ከሚቀርበው ብድር 90.70% (151,968,569.00) ከቁጠባ በመሰብሰብ አቅርቦቱን ማሳደግ ታቅዶ ክንዉን ብር 318,386.77 (0.2%) ብቻ ነዉ፤

12. በ2006፣ በ2008 እና በ2009 በጀት አመታት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በአበዳሪ ተቋሙ የሚቀርበዉን ብድርና ከቁጠባ በመሰብሰብ አቅርቦቱን ለማሳደግ የተያዘውን እቅድ የሚሳይ መረጃ በተደራጀ መልኩ በኦዲት ወቅት ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ፤

13. በ2007 በጀት አመት ብድር ሥርጭትን በተመለከተ በበጀት አመቱ በመንግሥት ዋስትና ብር 52,093,174.00 ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 7,197,350.00 (13.8%) ብቻ የተፈጸመ መሆኑ፤ የሚሉት መገለጫዎች በስራ እድል ፈጠራ፤ትስስር፤ ስልጠናና በድጋፍ ዙሪያ የተፈጸሙት ተግባራት የሚጠበቀውን ደረጃ (ስታንዳርድ) ለማሳካት የማያስችሉ መሆኑን ያሳያል።

## II. በእንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ የእንስሳት ጤና አገልግሎት፤ መድሃኒት አጠቃቀምና ስርጭትን በተመለከተ፤

14. **በወረዳ፣ ከተማና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮችና ኬላዎች ለእንስሳት ህክምና ስራ የሚያስፈልጉ የህክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶች (ማይስክሮስኮፕ፣ ሪኤጀንቶች፣ ወዘተ) ተሟልተዉ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል**፤ ይሁን እንጅ ኦዲት ሲደረግ፡-

**ሰሜን ሸዋ ዞን**

14.1 በሞጃና ወደራ ወረዳ የሚገኘዉ የወረዳዉ የእንስሳት ክሊኒክ ዉስጥ 2 ማይስክሮስኮፕ በተለይም አንደኛዉ ማይስክሮስኮፕ ከመጣ ጀምሮ እንደታሸገ ከ1999 በጀት ዓመት ጀምሮ ከአስር ዓመት በላይ በክሊኒኩ ዉስጥ የሚገኝ ቢሆንም በላብራቶሪ የታገዘ የህክምና አገልግሎት በክሊኒኩ ዉስጥ አለመሰጠቱ፤

14.2 በዞኑ ከ281 የእንስሳት ክሊኒኮች ዉስጥ 223ቱ (79.35%) የበሽታዎች መመርመሪያ ማይስክሮስኮፕ የሌላቸዉ መሆኑ፤

14.3 ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ በዞኑ ባሉ የእንስሳት ክሊኒኮች ዉስጥ በብልሽት ምክንያት (ማኮላሻ መሳሪያ 207፣ ፍሪጅ 22፣ ማይስክሮስኮፕ 7፣ የእንስሳት ኪኒን ማዋጫ 8፣ ተንቀሳቃሽ ፍሪጅ 4 እና ሲሪንጅ 16)፤ አገልግሎት የማይሰጡ 264 የህክምና መሣሪያዎች ተገኝተዋል፡፡

**በአዊ ብሔረሰብ ዞን**

14.4 በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ በወንጀላ እና በባጉና ቀበሌዎች የሚገኙ የእንስሳት ክሊኒኮች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ለኦዲት እስከተደረሰበት ቀን 5/3/2010 ዓ.ም ድረስ ከ4 ዓመት በላይ የህክምና እቃዎችና የክትባት ቁሳቁሶች ሳይቀቀሉና ሳይጸዱ አገልግሎት እየሰጡ መገኘታቸዉ፤

14.5 በዞኑ በ2009 በጀት ዓመት በስድስት ወረዳዎች (ዳንግላ፣ ፋግታ ለኮማ፣ ጓጉሳ ፣አንከሻ ፣ዚገምና ጃዊ ወረዳዎች)በሚገኙ የእንስሳት ክሊኒኮች ዉስጥ ብዛታቸዉ 828 የሚሆኑ የህክምና ቁሳቁሶች /መሣሪያዎች/ አገልግሎት የማይሰጡ በመሆኑ ተገቢዉን የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የተቸገሩ መሆኑ መታወቁ፣

14.6 በዞኑ የወረዳና የቀበሌ እንስሳት ክሊኒኮች ብዛት 147 ሲሆኑ ከዚህ ዉስጥ 125 (85%) የሚሆኑት ክሊኒኮች አስፈላጊ የሆኑ የህክምና ቁሳቁሶች /መሣሪያዎች/ የሌላቸዉ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

ይህም በተጠቀሱት አካባቢዎች (ዞን፤ወረዳዎችና ቀበሌዎች/ የሚገኙ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮችና ኬላዎች ለእንስሳት ህክምና ስራ የሚያስፈልጉ የህክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶች (ማይስክሮስኮፕ፣ ሪኤጀንቶች፤ የክትባት ቁሳቁሶች ወዘተ) ያልተሟሉላቸው እና የተሟሉትም ቢሆን አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነ ሲያመለክት ለህብረተሰቡ የሚቀርበው አገልግሎት ያልተሟላና ችግር ፈቺ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

15. **በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ ወረዳና በእያንዳንዱ ቀበሌ አንድ የእንስሳት ክሊኒክ (ጤና ኬላ) ሊገነባና ባለሙያ ተሟልቶላቸዉ አስፈላጊዉን የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡** ይሁን እንጅ ይህ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፡-

**ክልል እንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ**

15.1 በክልሉ ከ2005 እስከ 2009 ባሉት አምስት በጀት ዓመታት 4,768 የበሽታ ምልክቶች (ፍንዳታ) ተከስቶ 488,799 እንስሳት የታመሙ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥም 43,641 (8.92%) እንስሳት ለሞት ተዳርገዋል፡፡

15.2 በክልሉ ከ2005—2009 ባሉት 5 የበጀት ዓመታት የተለያዩ እንስሳት (ዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል፣ጋማ ከብት እና ዶሮዎች) ከታመሙት ብዛት 241,687,751 መካከል 280,645 (0.12%) እንስሳቶች ህክምና ሳያገኙ በመሞታቸዉ ክልሉ በነበረው የገበያ ዋጋ ግመታ ብር 58,966,822.00 ገንዘብ ሊያጣ መቻሉ፤

**ሰሜን ሸዋ ዞን**

15.3 በዞኑ በ2009 በጀት ዓመት ከጠቅላላዉ 24 ወረዳዎች ዉስጥ 9 (37.5%) ወረዳዎች በየቀበሌያቸዉ የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ መገንባት እያለባቸዉ ሳይገነቡ የተገኙ መሆኑ፣ (ግሼራቤል፣ መንዝ ላሎ፣

አንኮበር፣ ጣርማበር፣ አንጎለላናጠራ፣ በረኸት፣ ሲያደብርና ዋዩ፣ ሞረትና ጅሩ፣ ሚዳ ወረሞ፣ አንሳሮ እና መርሃ ቢቴ ወረዳዎች)፤

15.4 በሰሜን ሸዋ ዞን ባሉ ወረዳዎች ዉስጥ በየቀበሌዉ የእንስሳት ክሊኒክ /ጤና ኬላ/ ተገንብቶ አገልግሎት መስጠትና ሽፋኑንም ወደ 100% ማድረስ ያለበት ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት በዞኑ ያለዉ የክሊኒክ ግንባታ ሽፋን 60% ላይ ብቻ የሚገኝ መሆኑ፣

15.5 በዞኑ በ2009 በጀት ዓመት የቀበሌ የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ ለመገንባት ከ24ቱ ወረዳዎች 12ቱ (50%) *(ግሼ፣መንዝ ላሎ፣ ሞጃና ወደራ፣አንኮበር፣ጣርማ በር፣ኤፋራታና ግድም፣አንጎለላና ጠራ፣በረኸት፣ ሲያደብርና ዋዩ፣ ሞረትና ጅሩ፣ ሚዳወረሞ እና አንሳሮ)* ወረዳዎች እቅድ ቢይዙም ወደ ግንባታ ስራ ያልገቡ መሆናቸዉ፣

15.6 በዞኑ በ2009 በጀት ዓመት የእንስሳት ክሊኒክ ግንባታ በጣቢያ ደረጃ ዕቅድ 59 የተያዘ ሲሆን ክንዉን ደግሞ 26 (44.07%) ብቻ መሆኑ፤

15.7 በዞኑ 24 የእንስሳት ክሊኒኮች ተገንብተዉ ለአገልግሎት ዝግጁ ቢሆኑም ባለሙያ ስላልተመደበላቸዉ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፤ ለመገለጫም በ2008 በጀት ዓመት በሞጃና ወደራ ወረዳ በጉይ ቀበሌ ተሰርቶ የተጠናቀቀዉ የእንስሳት ክሊኒክ ከ2 ዓመት በላይ፤ በአይሶፌ ቀበሌ የተገነባዉ የእንስሳት ክሊኒክ ከ1/7/2009 ዓ.ም ጀምሮ እና በብርቃ ቀበሌ የተገነባዉ የእንስሳት ክሊኒክ ከ1/3/2009 ዓ.ም ጀምሮ በየተቋሞቹ ባለሙያ ባለመኖሩ/ባለመመደቡ ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው፤

15.8 በ2009 በጀት ዓመት በግሽራቤል ወረዳ 5 ቀበሌዎች እንዲሁም በመንዝ ላሎ በወረዳ ደረጃም የእንስሳት ክሊኒክ የሌለውና በዚሁ ወረዳ በ4 ቀበሌዎች ላይም የእንስሳት ጤና ኬላ ግንባታ ያልተሰራ መሆኑ፣

15.9 በአጠቃላይ በዞኑ 388 ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ በ129 (33.25%) ቀበሌዎች የእንስሳት ክሊኒክ ያልተገነባባቸዉ መሆኑ የሚሉት በኦዲት ተረጋግጠዋል፡፡

**16. የእንስሳት መድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸዉ ከማለፉ በፊት በየደረጃዉ ላሉ የሚመለከታቸዉ አካላት በማሳወቅ ጥቅም ላይ ማዋል ይህ ካልተቻለም በአወጋገድ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን በተመለከተ** ኦዲት ሲደረግ፡-

**ክልል ኤጀንሲ**

16.1 በክልሉ ከሁሉም ዞኖች በተገኘ መረጃ መሰረት ከ2005-2009 ባሉት አምስት በጀት ዓመታት ብር 7,160,074.81 የሚያወጡ የተለያዩ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥቅም ላይ ሳይዉሉ የአገልግሎት ዘመናቸዉ ያለፈባቸው መሆኑ፤

**ሰሜን ሸዋ ዞን**

16.2 በ2009 በጀት ዓመት በሰሜን ሸዋ ዞን በአብዛኞቹ ወረዳዎች በመንግስት የእንስሳት ክሊኒኮች የሚሸጠዉ መድሃኒት ከግል እንስሳት መድሃኒት ቤቶች ጋር ዋጋዉ ሲነጻጸር የግል መድሃኒት ቤቶች በአነስተኛ ዋጋ ስለሚሸጡ ተጠቃሚዉ ማህበረሰብ ከግል መድሃኒት ቤቶች መድሃኒቶችን እየገዛ የሚጠቀም በመሆኑ በዚህ ምክንያት በመንግስት ክሊኒኮች ያሉ መድሃኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸዉ እያለፈባቸዉ መሆኑ፤

16.3 በ2009 በጀት ዓመት በተለያዩ ወረዳዎች የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሃኒቶች እንዲያስወግዱ ቢገለፀም ከ24 ወረዳዎች ዉስጥ 9 (37.5 %) ወረዳዎች *(መንዝ ማማ፣ ሀገረ ማርያም፣ ሞረትና ጅሩ፣ መንዝ ላሎ፣ አሳግርት፣ መንዝ ቀያ፣ ጣርማ በር፣ ሲያደብርና ዋዩ፣ ባሶናወረና ወረዳዎች)* በመጋዝን አከማችተው ለረጅም ጊዜ ማለትም ከ2000 - 2009 ዓ.ም ድረስ ያስቀመጡ መሆኑ፤

16.4 በዞኑ ከ2005-2009 ባሉት 5 የበጀት ዓመታት ብር 407,395.00 የሚያወጡ የተለያዩ የእንስሳት መድሃኒቶች አገልግሎት ሳይሰጡ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈባቸው መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

**በአዊ ብሔረሰብ ዞን**

16.5 ከ2005-2009 ባሉት 5 የበጀት ዓመታት በአዊ ዞን በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ብዛታቸዉ 153,271 የሆነ የእንስሳት መድሃኒቶችና ክትባቶች በድምሩ ብር 219,002.25 በመመሪያው መሠረት እንዲወገዱ ባለመደረጉ እስቶር ክፍል እያጣበቡ መሆናቸዉ፤ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

**17. የእንስሳት ክሊኒክና መድሃኒት ንግድ የሙያ ፈቃድ የተሰጠዉ/ጣት ግለሰብ /የእንስሳት ህኪምና መድሃኒት ባለሙያ/ በሌለበት ሁኔታ በደብረ-ብርሃን እና በእንጅባራ ከተሞች የተለያዩ የገጠር እንስሳት መድሃኒት ቤቶች የእንስሳት መድሃኒት ንግድ እንደሚያካሂዱ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡**

## III. የአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ በደን ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀም በተመለከተ፤

### 18. የችግኞችን ጽድቀት መጠን በተመለከተ፤

18.1 **በኢንተርፕራይዙ በየበጀት አመቱ የሚተከሉ ችግኞች አመታዊ የሁለተኛ ዙር (ከመጋቢት እስከ ግንቦት ወር) አማካኝ የችግኝ የጽድቀት መጠናቸው 80% እና በላይ መሆን እንዳለበት አለም አቀፍ የችግኝ የጽድቀት ደረጃ (ስታንዳርድ) ይገልጻል፡፡** ይህን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተለው ተስተውሏል፡-

18.2 ኢንተርፕራይዙ ላይ በተገኙ **የሰነድ ማስረጃዎች** በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶቹ ከ2004/2005 እስከ 2008/2009 ባሉት 5 የበጀት አመታት በጠቅላላው **29,844,681** ልዩ ልዩ አይነት የችግኝ ዝርያዎች ተተክለው የጸደቁት ግን **17,945,807 (60%)** ችግኞች ብቻ መሆናቸው፤

18.3 ከላይ በተራ ቁጥር 18.1 እና 18.2 የተገለጸውን የችግኞች የጽድቀት መጠን በአካል ቆጠራ ለማረጋገጥ በቅ/ጽ/ቤቶቹ በ2008/2009 በጀት ዓመት የተተከሉ ችግኞች በሰነድ ላይ የተገኙ የቆጠራ መረጃዎች በደ/ታቦር በ2 የተከላ ቦታዎች፣ በእንጅባራ በ3 የተከላ ቦታዎች፣ በደ/ማርቆስ በ3 የተከላ ቦታዎች በጠቅላላው ከተተከሉት **283,193** ችግኞች **165,349 (58.37%)** እንደጸደቁ በቅ/ጽ/ቤቶች ቆጠራ ተደርጎ በሰነድ የተገኙ ሲሆን የኦዲት ቡድኑ በተከላ ቦታዎቹ ላይ 2% ናሙና በመውሰድ በተደረገው ቆጠራ

ጸድቀው የተገኙት 92,718 (32.7%) ብቻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህን የኦዲት ግኝት መነሻ በማድረግ ኢንተርፕራይዙ በላከው የኦዲት ምላሽ የጸደቃ መጠኑ 55% መሆኑ ቢገለጽም በክትትል ኦዲት እስከሚረጋገጥ ድረስ በኦዲት ግኝት የተደረሰበት የጸደቃ መጠን 32.7%**ብቻ** መሆኑን (ዝርዝር መረጃው ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡)

**ሰንጠረዥ ቁጥር 1 በቅ/ጽ/ቤቶች በሰነድ የተገኙና በኦዲት ቡድኑ በቆጠራ የተገኙ የችግኝ ጽድቀት መጠን**

| በቅ/ጽ/ቤቶቹ በሰነድ የተገኘ የቆጠራ ውጤት | | | | | | በኦዲት ቆጠራ የተገኘ ውጤት | | ልዩነት ቅ/ጽ/ቤቱ ጸድቋል ያለው በመብለጥ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቆጠራ ቀን | ቅ/ጽ/ቤቱ | የተከላ ቦታ | የተተከለ | የጸደቀ | አማካኝ | የጸደቀ | አማካኝ | |
| 7/12/2009 | ደ/ታቦር | ላ/ጋይንት ዋቲ | 76,743 | 33,767 | 44% | 14,427 | 18.18% | 19,340 |
| 9/12/2009 | | ሊቦ-ግራርጌ | 56,793 | 28,731 | 51% | 16,981 | 29.97% | 11,750 |
| **የደብረ ታቦር ድምር** | | | **133,536** | **62,498** | **46.8** | **31,408** | **23.52** | **31,090** |
| 01/3/2010 | እንጅባራ | ዳንግላ - መንደር 4 | 30,123 | 22,593 | 75% | 9,507 | 31% | 13,386 |
| 06/3/2010 | | ጓንጓ - ዘገየ ተራራ | 31,949 | 11,821 | 37% | 2,796 | 8.75% | 9,025 |
| 04/3/2010 | | ባንጃ - ዘንገና | 8,979 | 3,501 | 39% | 1,347 | 15% | 2154 |
| **የእንጅባራ ድምር** | | | **71,051** | **37,915** | **53.36** | **13,650** | **18.2%** | **23368** |
| 12/4/2010 | ደ/ማርቆስ | ሰዴ - ለባሴ | 41,500 | 32,387 | 78% | 18,442 | 44.44% | 13,945 |
| 13/4/2010 | | ደ/ማ- የራባ | 2,626 | 2,206 | 84% | 2,600 | 99% | 394 በማነስ |
| 17/4/2010 | | አነደድ -የቁር ገች | 34,480 | 30,343 | 88% | 26,618 | 77.2% | 3,725 |
| **የደብረ ማርቆስ ድምር** | | | **78,606** | **64,936** | **82.6%** | **47,660** | **60.6%** | **17276** |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | **283193** | **165,349** | **58.38%** | **92718** | **32.7%** | |

18.4. ከ2004/2005 እስከ 2008/2009 በጀት አመት ኢንተርፕራይዙ በሁሉም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ብር 2,967,296 ወጭ ወጥቶባቸው በ 1717.19 ሄ/ር መሬት ላይ የተተከሉ 4,045,731 ልዩ ልዩ የዛፍ ችግኞች የ2ኛ ዙር ቆጠራ በተደረገበት በጀት አመት አማካኝ የችግኝ ጽድቀት መጠናቸው ከ25% በታች በመሆናቸው የተከላ ቦታዎቹ ተከላ በተደረገበት በጀት ዓመት ሙሉ ተከላ የሚያስፈልጋቸው ሁነው መገኘታቸው፤

18.5 በኦዲት በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2004/2005 እስከ 2008/2009 በተተከሉበት በጀት አመት የ2ኛ ዙር ቆጠራ ሲደረግ በ 376.9 ሄ/ር መሬት ላይ ብር 1,293,453.91 የወጣባቸው 1,072,926 ልዩ ልዩ ችግኞች አማካኝ የጽድቀት መጠናቸው **ከ25%** በታች በመሆኑ ተከላ በተደረገበት በጀት ዓመት ሙሉ ተከላ የሚያስፈልጋቸው ሁነው መገኘታቸው፤

## 19. የችግኝ ብክነትና ለተከላ ብቁ መሆናቸውን በተመለከተ፣

19.1 ኢንተርፕራይዙ በየበጀት አመቱ መጨረሻ በራሱ የሚያፈላቸው እና ችግኝ አፍልተው በመሸጥ ከተደራጁ የአረንጓዴ ኢተርፕራይዞች ግዥ ፈጽሞ የሚተክላቸው ችግኞች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ለተከላ ብቁ እና አለም አቀፍ የችግኝ ብክነት ስታንዳርድ ከ10% በታች መሆን እንዳለባቸው የኢንተርፕራይዙ ስትራቴጅክ እቅድ ላይ ተመልክቷል፡፡ የዚህን ውጤታማነት ለመገምገም ኦዲት ሲደረግ የሚከተለው ተስተውሏል፡፡

**በችግኝ ጣቢያዎች የከረሙ ችግኞችን በተመለከተ፤**

**ደ/ታቦር ቅ/ጽ/ቤት**

19.2 በ2007/2008 በላይ ጋይንት ወረዳ ዳሞት፣ በፎገራ ወረዳ ቋህር፣ በሊቦ ከምከም ወረዳ ሽምችና በስማዳ ወረዳ በወገዳ የመደበኛ ችግኝ ጣቢዎች 306,507 ልዩ ልዩ ችግኞች የፍል ጊዜያቸውን ባለመጠበቃቸው በተፈሉበት በጀት አመት መጨረሻ ለተከላ ብቁ ባለመሆናቸው በችግኝ ጣቢያዎቹ ውስጥ ለተጨማሪ አንድ አመት የከረሙ መሆናቸው፤

19.3 በ2009 በጀት አመት በፎገራ ወረዳ በቁሃር ችግኝ ጣቢያ ከተፈላው 39,930 የዲከረንስ ችግኝ ውስጥ በአመቱ መጨረሻ 27,951(71.68%) ችግኞች ያልተተከሉ መሆናቸው፤

19.4 በ2008 በጀት አመት በላይ ጋይንት ወረዳ በዳሞት ችግኝ ጣቢያ የቅድመ ስራው በጥቅምት/2008 ተጀምሮ መፈላት ሲገባው በመጋቢት/2008 በመፈላቱ በችግኝ ጣቢያው ከ6 እስከ 7 ወር መቆየት የነበረበት 14,770 የነጭ ባህር ዛፍ ችግኝ በቀን 27/10/2009ዓ.ም የኦዲት ቡድኑ በአካል በቦታው በተገኘበት ጊዜ ለ1 አመት ከስድስት ወር በችግኝ ጣቢያው ውስጥ ከርመው መገኘታቸው፤

19.5 በ2009 በጀት አመት በላይጋይንት ወረዳ በዳሞት ችግኝ ጣቢያ የቅድመ ስራው በጥቅምት/2009 ጀምሮ መዘራት የነበረበት በመጋቢት/2009 በመዘራቱ በችግኝ ጣቢያው ውስጥ 55,495 በብትን የተዘሩ የነጭ ባህር ዛፍ ችግኞች ለተከላ ባለመድረሳቸው ለተጨማሪ 1 አመት እንዲከርም መደረጉ፤

**እንጅባራ ቅ/ጽ/ቤት**

19.6 ከ2005 እስከ 2009 በጀት አመት በዲንካራና ስጋዴ የመደበኛ ችግኝ ጣቢያዎች በአመቱ መጨረሻ ላይ ለተከላ ያልደረሱ /ብቁ ያልሆኑ/ 1,009,847 ልዩ ልዩ ችግኞች ለተጨማሪ አንድ አመት በችግኝ ጣቢያዎቹ በመከረማቸው ብር 20,196.94 ቅ/ጽ/ቤቱን ወጭ ያስወጣው መሆኑ፤

19.7 ከ2005 እስከ 2009 በጀት አመት ከተፈላው ከጠቅላላ 10,550,520 ልዩ ልዩ ችግኞች ውስጥ 4,034,864 (38.2%) ችግኞች በችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ፣ በችግኝ ማጓጓዝና በተከላ ወቅት መባከናቸው ይህም ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 2,420,918.40 ለኪሳራ የዳረገ መሆኑ፤

**ደብረማርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

19.8 በ2008 በጀት አመት በችግኝ ማፍላት ከተደራጁ የአረንጓዴ ኢንተርፕራይዞች ግዥ ከተፈጸመባቸው 364,042 የነጭ ባህርዛፍ ችግኞች መካከል 75,157 (20%) ችግኞች ሳይተከሉ መባከናቸው እና ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 47,348.98 ለኪሳራ የዳረገ መሆኑ፤

19.9 ከ2006/2007 እስከ 2008/2009 በጀት አመታት ከተፈላው 6,021,643 ልዩ ልዩ ችግኞች 784,821(13%) ችግኞች በችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ፣ በችግኝ ማጓጓዝና በተከላ ወቅት መባከናቸው እና ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 470,892.60 ለኪሳራ መዳረጉ፤

**22. ለችግኝ መትከያ የሚቆፈሩ ጉድጓዶችን በተመለከተ፣**

22.1 በየበጀት አመቱ ኢንተርፕራይዙ ለችግኝ መትከያ በሚቆፈሩ ጉድጓዶች ሙሉ በሙሉ ችግኞች መተከል እንዳለባቸው በኢንተርፕራይዙ ስትራቴጅክ እቅድ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ይህን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የሚከተለው ተስተውሏል፡-

**ደብረታቦር ቅ/ጽ/ቤት**

22.2 በ2008/2009 በጀት አመት በእስቴ፣ ስማዳ፣ ሊቦ፣ እብናት፣ አንዳቤት፣ ፎገራና ላይጋይንት ወረዳዎች ለአዲስ የችግኝ መትከያ የሚሆን 187,947 የችግኝ ጉድጓዶች፣ ለማጠናከሪያ ተከላ የሚሆን 1,343,816 የችግኝ ጉድጓዶች በድምሩ 1,531,763 የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች ተቆፍረው 27,886 በአዲስ ከተቆፈሩት፣ 35,142 ለማጠናከሪያ ከተቆፈሩ በድምሩ 62,886 የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች ውስጥ ችግኞች አለመተከላቸውና በዚህም ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 31,443.00 ለኪሳራ የዳረገ መሆኑ፤

**እንጅባራ ቅ/ጽ/ቤት**

22.3 ከ2005/2006- 2009/2010 ባሉት አምስት በጀት አመታት ለችግኝ መትከያ ተቆፈረው ከተዘጋጁ 4,821,504 የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች 476,725 ጉድጓዶች ችግኝ ሳይተከልባቸው መቅረቱ እና በዚህም ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 238,362.50 ለኪሳራ የዳረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

**ደብረማርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

22.4 በ2007 እና 2008 በጀት አመት በጠቅላላው 246,919 ለልዩ ልዩ ችግኞች መትከያ የተቆፈሩ ጉድጓዶች በችግኝ መትከያ ወቅት ችግኞች ሳይተከሉባቸው መቅረታቸውና በዚህም ቅ/ጽ/ቤቱን ብር 123,459.50 ለኪሳራ የዳረጉ መሆናቸው፤

22.5 በኦዲት በታዩት በሶስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ከ2006 እስከ 2008 በጀት አመት ለችግኝ መትከያ የተቆፈሩ 828,558 የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች ችግኞች ሳይተከሉባቸው በመምከናቸው ኢንተርፕራይዙ ብር 414,273.70 ለኪሳራ የተዳረገ መሆኑን ተመልክቷል፡፡

**23. ኢንተርፕራይዙ የ2ኛ እና የ3ኛ ደረጃ /እሴት የተጨመረባቸው/ ምርቶችን አምርቶ ለገበያ እያቀረበ በገቢ እቅዱ መሰረት ገቢውን እያሳደገ እና የውጭ ምንዛሪ ገቢ እያስገኘ መሆኑን በተመለከተ፤**

**በኢንተርፕራይዙ ዋና መ/ቤት**

23.1 ኢንተርፕራይዙ ከተቋቋመበት ከ2002 ዓ.ም አንስቶ የ2ኛ ደረጃ እና የ3ኛ ደረጃ ምርቶችን አምርቶ ለውጭ ገበያ አላቀረበም፣ የተገኘ /የተሰበሰበ/ የውጭ ምንዛሪም የለም፤

23.2 ከ2005 እስከ 2009 ከ2ኛ ደረጃ ደንና የደን ምርት ውጤቶች ብር 143,590,457.00 ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ የተሰበሰበው ገቢ ብር 73,991,591.00 (51.53%) ብቻ መሆኑ፤

23.3 ከ2005-2009 በጀት አመታት መሰረታዊ የ2ኛ ደረጃ ምርቶች ከሆነው የጣውላ ምርት ብር 12,574,672.80 ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ከንውኑ ብር 6,301,307.90 (50.11%) ብቻ ነው፤

**ደብረ ታቦር ቅ/ጽ/ቤት**

23.4 በ2009 በጀት አመት በቅ/ጽ/ቤቱ ከሁለተኛ ደረጃ ምርት ውጤቶች ብር 1,795,939.65 ገቢ ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ምንም ባለመከናወኑ የአመቱ የገቢ እቅድ ክንውኑ 0% መሆኑ፤

23.5 የእንጨት መሰንጠቂያ ፋብሪካው የኤሌክትሪክ ሃይሉ የከተማው ማህበረሰብ መብራት ከሚያገኝበት ትራንስፎርመር ቀጥታ የተሳበና ፋብሪካው ስራ ላይ ሲሆን ከማህበረሰቡ ላይ ከሚደርሰው ጫና በተጨማሪ ፋብሪካውን ለማንቀሳቀስ የሃይል እጥረት ያለበት መሆኑ፤

**በእንጅባራ ጣውላ ፋብሪካ**

23.6 በ2009 በጀት ዓመት ለ318 ሰዓት ወይም 39.75 ቀናት በመብራት መቋረጥ ምክንያት ፋብሪካው ማምረት የነበረበትን 278.25 ሜ/ኩብ ጣውላ ባለማምረቱ ቅ/ጽ/ቤቱ በጥቅል ከብር 1,740,000.00 በላይ ያልተጣራ ገቢ ያሳጣው መሆኑ፣ *(በ1 ሰዓት የሚመረት 0.875 ሜ/ኩብ ጣውላ* 318 ሰዓት ጠቅላላ ያልተሰራበት=278.25ሜ/ኩብ) *የ1ሜ/ኩብ ጣውላ አማካኝ ዋጋ ብር 6,253.40= 1,740,000)*፤

23.7 የእንጨት መሰንጠቂያ ፋብሪካው የማምረት ስራ ከጀመረበት ጥር 2008 አንስቶ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኑ ችግር ያለበት መሆኑ ቀሪ የማስተካከል ስራዎችን ሳይሰሩ የመያዣ ሂሳቡ ተለቆለት ችግሩ መፍትሄ ያላገኘ መሆኑ፤

**ደብረማርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

23.8 ከ2006 እስከ 2009 ከሁለተኛ ደረጃ ምርቶች ብር 55,742,743.83 ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ የተሰበሰበው ገቢ ብር 32,880,181.72 /58.98%/ ብቻ መሆኑ፤

23.9 ከ2006 እስከ 2009 በጀት አመት ከጣውላ ምርት ብር 42,783,368.00 ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ የተሰበሰበው ብር 26,664,943.66 ሲሆን አፈጻጸሙ /62.32%/ መሆኑ፤

23.10 ለእንጨት መሰንጠቂያ ፍብሪካው መቅረብ እያለባቸው ያልቀረቡ መሰረታዊ የፍብሪካ መለዋወጫ እቃዎች መኖራቸው፤

23.11 የጣውላ ፋብሪካው ከ2006- 2009 ባሉት 4 በጀት ዓመታት በመብራት መቆራረጥ 1,155 ሰዓት በማሽን ብልሽት 1,242.34 ሰዓት በድምሩ 2,397.34 ሰዓት በመባከኑ ማምረት የነበረበትን 2,397.34 ሜ/ኩብ ጣውላ ባለማምረቱ ቅ/ጽ/ቤቱ በጥቅል ሽያጭ ብር 14,556,456.70 ገቢ ያጣ መሆኑ በኦዲትተረጋግጧል፡፡*(በ1 ሰዓት የሚመረት ጣውላ 1ሜ/ኩብ* 2,397.34 ጠቅላላ ያልተሰራበት ሰዓት=መመረት የነበረበት 2,397.34 ጣውላ በሜ/ኩብ)* የ1 ሜ/ኩብ ጣውላ አማካኝ ዋጋ ብር 6,071.92 =14,556,456.70)፤*

ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች የሚያሳዩት በኢንተርፕራይዙ የደን ልማት፣አስተዳደርና ገቢ የማስገኘት ዓላማዎች በሚጠበቀው ደረጃ ያልተሳኩና በታቀደው መጠን ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ ያላስገኘ እና ውጤታማ አለመሆኑን ያመለክታሉ፡፡

## IV. በመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የሁሉን አቀፍ ገጠር መንገድ ተደራሽነት (URRAP) ፕሮግራም፤

### 24. በተቋራጭ ማህበራት ውል ከተያዘ በኋላ ያልተጠናቀቁ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

በሁሉን አቀፍ የወረዳ ገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የተሰሩ ፕሮጀክቶች የመንገድ ግንባታ የመሬት ስራቸው በተዘጋጀላቸው ዲዛይንና በተገባው ውለታ መሰረት መከናወኑንና መጠናቀቁን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

**ምስራቅ ጎጃም ዞን**

24.1 **በእነብሴ ሳር ምድር** ወረዳ በ2004 በጀት ዓመት በፕሮጀክት ዋጋ ብር 9,773,737.66 ወጪ የተደረገበት የመርጦ ለማርያም-ቀንዳች ፕሮጀክት በውሉ መሰረት ስራው በተጀመረበት በጀት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ከአጠቃላይ ርዝመቱ 15.4 ኪ.ሜ ውስጥ 1.7 ኪ.ሜትሩ ሳይሰራ ከ5 ዓመት በላይ የዘገየና ያልተሰራ መሆኑ፤

24.2 **በባሶ ሊበን** ወረዳ በፕሮጀክት ዋጋ ብር 3,168,000.00 ታቅዶ ወደ ስራ ሲገባ ብር 3,665,135.19 ወጪ የተደረገበት የቤተንጉስ-ኮሜዘሜ ፕሮጀክት በ2006 ዓ.ም ግንባታው የተጀመረና በውሉ መሰረት ስራው በተጀመረበት በጀት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ከ11.92 ኪ.ሜ ውስጥ 1.30 ኪ.ሜትሩ የመሬት ቆረጣና ድልዳሎ ስራው ከ3 ዓመት በላይ የዘገየና ያልተሰራ መሆኑ፤

24.3 **በሁለት እጁ እነሴ** ወረዳ በፕሮጀክት ዋጋ ብር 8,310,034.49 በ2007 በጀት ዓመት የተጀመረውና ብር 3,958,762.88 ወጪ የተደረገበት የዘላለም ደስታ-ጮቄ ፋና ፕሮጀክት በውሉ መሰረት ስራው በተጀመረበት በጀት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም ከአጠቃላይ ርዝመቱ 12.10 ኪ.ሜ ውስጥ 4.10 ኪ.ሜትሩ ጠጠር ማልበስ ስራው ሳይሰራ ከ2 ዓመት በላይ የዘገየና ያልተሰራ መሆኑ፤

24.4 **በጎንቻ ሲሶ እነሴ** ወረዳ በድምሩ በፕሮጀክት ዋጋ በብር 4,528,000.00 ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት፣በድምሩ ብር 2,343,679.79 ወጪ የተደረገባቸው በ2006 ዓ.ም

የተጀመረው **የጌቴ ሰማኔ-እነዘባ** ፕሮጀክት ከ6.00 ኪ.ሜ ውስጥ 3.00 ኪ.ሜትሩ ሳይሰራ ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ እንዲሁም በ2007 ዓ.ም የተጀመረው **የትግዳር-መርሃጎፋን** ፕሮጀክት ከ5.53 ኪ.ሜ ውስጥ 2.88 ኪ.ሜ ጠጠር የማልበስ ስራ ሳይሰራ ከ2 ዓመት በላይ የዘገየና ያልተጠናቀቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**ስናን ወረዳ**

24.5 ግንባታቸው በ2007 ዓ.ም የተጀመረው፣ በድምር የፕሮጀክት ዋጋ ብር 8,360,000.00 በዛው ዓመት መጠናቀቅ የነበረባቸውና ብር 6,258,612.22 ወጪ የተደረገባቸው የገዳማዊት-ጦማዊት ፕሮጀክት ከ9.46 ኪ.ሜ ውስጥ 6.73 ኪ.ሜትሩ፣የዋሻ መንገድ-ደብረ ዘይት ፕሮጀክት ከ5.20 ኪ.ሜ ውስጥ 2.00 ኪ.ሜትሩ ጠጠር የማልበስ ስራ ሳይሰሩ ከ2 ዓመት በላይ ግንባታቸው የዘገየ መሆኑ፤

24.6 ግንባታቸው በ2006 ዓ.ም የተጀመረው፣በዛው ዓመት መጠናቀቅ የነበረበረባቸውና ብር 3,007,922.81 ወጪ የተደረገበት የጠጠር- ጠንዳሪ ፕሮጀክት ከ13.00 ኪ.ሜ ውስጥ 1.91 ኪ.ሜትሩ እንዲሁም የሮቡ ገበያ-ስናን ማርያም ፕሮጀክት ከ4.50 ኪ.ሜ ውስጥ 1.44 ኪ.ሜትሩ ሳይሰሩ ከ3 ዓመት በላይ ግንባታቸው የዘገየ መሆኑ፤

**ጎዛምን ወረዳ**

24.7 ግንባታው በ2007 ዓ.ም የተጀመረውና በዛው ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት **የደ/ማርቆስ-ደሳ እነሴ** ፕሮጀክት 2.50 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የመንገዱ አካል ከፍተኛ የመሬት ቆረጣና ድልዳሎ ስራ እንዲሁም የአፈር አቃፊ ግንብ /retaining wall/ ስራ የሚጠይቅና ከተቋራጩ አቅም በላይ በመሆኑ የግንባታ ስራው በውሉ መሰረት መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ ከ2 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፡

**ምዕራብ ጎጃም ዞን**

24.8 **በቡሬ** ወረዳ ግንባታው በ2008 ዓ.ም የተጀመረው፣8.64 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውና ብር 4,851,696.97 ወጪ የተደረገበት የአምባየ -አግኒ ፈረዳ ፕሮጀክት በውሉ መሰረት በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው አንድ ስላብ እና የስትራክቸር ስራ ሳይጠናቀቅ ከ2 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

24.9 **በቋሪት** ወረዳ በ2006 በጀት ዓመት የተገነባው **የአመድበር-ዋሚት** ፕሮጀክት በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው ከ6.92 ኪ.ሜ ውስጥ 2.62 ኪ.ሜትሩ ሳይሰራ የተቋረጠ መሆኑ፤

**ጎንጅ ቆለላ**

24.10 ግንባታቸው በ2006 ዓ.ም የተጀመረው፣ በድምሩ ብር 8,673,094.45 ወጪ የተደረገባቸውና 35.60 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው 3 ፕሮጀክቶች (ዋሸራ-ቅ/ገብርኤል-ደብረ መድሃኒት-አበድራይ፣ ዋሸራ-ከንቸችል-አቅሌ እና አቅሌ-ደባይ-አርዲሳ) ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸርና በ18 ሜትር ድልድይ ምክንያት ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

24.11 ግንባታቸው በ2008 ዓ.ም የተጀመረው፣በድምሩ ብር 3,839,765.94 ወጪ የተደረገባቸው 15.128 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው የይናጭ-ወለቂ-አንጎፌ እና የወለቂ-ዘማ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው በተጀመረበት

ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸርና በ40 ሜትር ድልድይ ምክንያት ከ1 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

**ሜጫ ወረዳ**

24.12 15.50 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው **የለሁሉም ሰላም-ጥሩ ሜዳ** ፕሮጀክት 3.85 ኪ.ሜትሩ በ2006 በጀት ዓመት በብር 883,333.34 እንዲሁም 2.146 ኪ.ሜትሩ ደግሞ በ2007 በጀት ዓመት በብር 710,663.60 የተሰራ ሲሆን ቀሪው 9.464 ኪ.ሜትሩ በመሬት አቀማመጡ ምክንያት ሳይሰራ ተቋረጠ ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

24.13 በ2006 በጀት ዓመት በብር 1,663,515.94 የተገነባው **የቆጋ ግድብ- ብርሀን ጮራ** ፕሮጀክት ከ9.00 ኪ.ሜ ውስጥ 1.455 ኪ.ሜትሩ ከ3 ዓመት በላይ ሳይሰራ የዘገየ ፣እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት የተገነቡት **የወተት ዓባይ -እድገት** ፕሮጀክት ከ10.00 ኪ.ሜ ውስጥ 2.50 ኪ.ሜትሩ እና **የፈለገ ብርሀን-ይነሳ ለምርት** ፕሮጀክት ከ8.00 ኪ.ሜ ውስጥ 2.00 ኪ.ሜትሩ ሳይሰሩ ከ1 ዓመት በላይ የዘገዩ መሆኑ፤

24.14 በ2006 ዓ.ም ግንባታቸው የተጀመረው፣ በድምሩ 19.87 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸውና ብር 5,165,606.86 ወጪ የተደረገባቸው 3 ፕሮጀክቶች (ከመርዓዊ-ቆለላ፣ከአማሪት-እድገት እና ከአማሪት-አዲስ አምባ) ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸርና በአነስተኛ ድልድይ አለመሰራት ምክንያት ስራው ከ3 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

24.15 በ2007 ዓ.ም ግንባታቸው የተጀመረው በድምሩ 14.378 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸውና ብር 3,985,132.68 ወጪ የተደረገባቸው 3 ፕሮጀክቶች (ከሁሉምሰላም-ዘመነ ብርሀን፣ ከጎራጎጥ-ታጠቅ እና ከአማሪት-እድገት) ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው የስተራክቸር ስራው ከ2 ዓመት በላይ በመዘግየቱ አለመጠናቀቁን፤

24.16 በ2008 ዓ.ም ግንባታው የተጀመረው፣ 9.06 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውና ብር 3,989,261.05 ወጪ የተደረገበት **የአዲስ አለም- አዲስ ልደት** ፕሮጀክት ግንባታው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በ12 ሜትር ድልድይ አለመሰራት ምክንያት ስራው ከ1 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

**ሰከላ ወረዳ**

**24.17** በ2005 በጀት ዓመት በብር 9,229,879.41 የተገነባው **የግሽ ዓባይ-ዘገዛ ፕሮጀክት** ከ11.37 ኪ.ሜ ውስጥ 7.00 ኪ.ሜትሩ ከ4 ዓመት በላይ የዘገየ እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት በብር 3,232,364.75 የተገነባው **የሳውሳ-ከበሳ ፕሮጀክት** ከ9.2 ኪ.ሜ ውስጥ 3.6 ኪ.ሜትሩ በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸርና በድልድይ ምክንያት ሳይሰራ ከ3 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

**24.18** በ2007 በጀት ዓመት በብር 1,982,456.46 የተገነባው **የገሬልታ-አሊቦ ፕሮጀክት** ከ11.02 ኪ.ሜ ውስጥ 7.02 ኪ.ሜትሩ ከ2 ዓመት በላይ የዘገየ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት በብር 4,739,996.21 የተገነባው **የከበሳ-አቢወትጮራ** ከ11.01 ኪ.ሜ ውስጥ 1.56 ኪ.ሜትሩ በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸር አለመሟላት ምክንያት ሳይሰራ ከ1 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

**ወምበርማ ወረዳ**

24.19 ግንባታቸው በ2005 ዓ.ም የተጀመረው በድምሩ 14.2 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸውና ብር 6,619,675.08 ወጪ የተደረገባቸው የሸንዲ-ጼንድ እና የሸንዲ-በሊማ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸር አለመሟላት ምክንያት ስራው ከ4 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

24.20 ግንባታቸው በ2006 ዓ.ም የተጀመረው በድምሩ 14.00 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸውና ብር 1,729,713.03 ወጪ የተደረገባቸው 3 ፕሮጀክቶች (የጎመር-ኮሊ፣ የወገዳድ-ማርወለድ እና የገዳድ-የርግን) ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸር አለመሟላት ምክንያት ስራው ከ3 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

**ጃቢጠህናን ወረዳ**

24.21 ግንባታው በ2005 ዓ.ም የተጀመረው፣ 16.9 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውና ብር 11,274,217.70 ወጪ የተደረገበት የፋኑተሰላም-ኩኒ አግቢ ፕሮጀክት ግንባታው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው መሠራት ከነበረበት 28 ስተራክቸር መካከል 6ቱ ሳይሰሩ ከ4 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤ /

24.22 ግንባታቸው በ2006 ዓ.ም የተጀመረውና በድምሩ 6.90 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው የቀረር-አባሰም እና የላይበር-ወይንማ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በውሃ ማፋሰሻ ስተራክቸር አለመሟላት ምክንያት ስራው ከ3 ዓመት በላይ መዘግየቱ፤

**ሰሜን ጎንደር ዞን**

24.23 **በምዕ/በለሳ** ወረዳ ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት፣ በድምሩ ብር 13,254,425.88 ወጪ የተደረገባቸው በ2005 ዓ.ም የተጀመረው የአርባያ-ሮቢት ፕሮጀክት ከ23 ኪ.ሜ ውስጥ 2 ኪ.ሜትሩ ከ4 ዓመት በላይ ሳይሰራ የተጓተተ እንዲሁም በ2007 ዓ.ም የተጀመረው የአርባያ-አይሰግ-ጎዛ ፕሮጀክት ከ19.226 ኪ.ሜ ውስጥ 3.00 ኪ.ሜትሩ ሳይሰራ ከ2 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

**ደባርቅ ወረዳ**

24.24 በ2006 ዓ.ም የተጀመረውና ብር 3,665,135.19 ወጪ የተደረገበት የምቅራና-አብርሃም ፕሮጀክት ከ20.00 ኪ.ሜ ዉስጥ 8.00 ኪ.ሜትሩ አለታማና ተንሸራታች በመሆኑ ግንባታው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው የመንገዱ ስራ ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

**ጎንደር ዙሪያ ወረዳ**

24.25 ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት፣ በድምሩ ብር 10,384,845.31 ወጪ የተደረገባቸው በ2006 ዓ.ም የተጀመረው የአስብሃ-ጉባይፕሮጀክት ከ5.778 ኪ.ሜ ውስጥ 3.478 ኪ.ሜትሩ ሳይጠናቀቅ ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ እንዲሁም በ2007 ዓ.ም የተጀመረው የማክሰኝት -ላይዱጌ ፕሮጀክት ከ11.85 ኪ.ሜ ዉስጥ 1.65 ኪ.ሜትሩ ስራው በማህበረሰብ ተሳትፎ አለመሟላት፤ለተቋራጭ ውል የተሰጠበት ጊዜ የዘገየ በመሆኑ፤ በውሃ ማፋሰሻ ስትራክቸርና በድልድይ አለመጠናቀቅ ምክንያት ከ2 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

***ደንቢያ ወረዳ***

24.26 ግንባታቸው በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ የነበረበት፣ በድምሩ ብር 5,974,837.69 ወጪ የተደረገበትና ግንባታው በ2006 ዓ.ም የተጀመረው የአባዉራም -ጎንትር ፕሮጀክት ከ13.70 ኪ.ሜ ዉስጥ 5.50 ኪ.ሜትሩ ሳይጠናቀቅ በተቋራጭ አቅም ማነስና በስተራክቸር አለመጠናቀቅ ምክንያት ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ ታውቋል፤

24.27 ግንባታው በ2005 ዓ.ም የተጀመረው፣ 10.00 ኪ.ሜ ርዝመት ያለውና ብር 5,524,617.09 ወጪ የተደረገበት የመስቀለ ክርስቶስ-አባዉራም ፕሮጀክት በተጀመረበት ዓመት መጠናቀቅ ሲገባው በማህበረሰብ ተሳትፎ አለመሟላትና በስትራክቸር አለመጠናቀቅ ምክንያት ከ4 ዓመት በላይ ስራው መዘግየቱ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 24.1- 24.27 የተዘረዘሩት መንገዶች ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት 24/04/2010 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተጠናቀቁ የግንባታ ስራዎች፤የስተራክቸር (ውሃ ማፈሰሻ ቦይ)፤ የጠጠር ማልበስ ስራ መቋረጥ፤ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ድልድዮች በየወቅቱ በእቅድና የስራ ፕሮግራም እየተካተቱ ባለመፈጸማቸው እና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች ግንባታቸው አለመጠናቀቃቸውን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በዚህም ምክንያት በርካታ (በዝርዝር ሪፖርቱ በተመለከቱት አካባቢዎች) በሁሉን አቀፍ የወረዳ ገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የተሰሩ ፕሮጀክቶች የተሟላ የክረምት ከበጋ አገልግሎት እየሰጡ የማይገኙበት ሁኔታ እና በርካታዎቹ ደግሞ በበጋ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 25. በበጋም ሆነ በክረምት አገልግሎት የማይሰጡ መንገዶችን በተመለከተ፤

***ምስራቅ ጎጃም ዞን***

25.1 **በባሶሊበን ወረዳ** በ2006 በጀት ዓመት የተገነቡ፣ በድምሩ ብር 5,747,967.09 ወጪ የተደረገባቸውና 19.98 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው **የዞንበል-ጫራ** እና **የቤተንጉስ-ኮሜዘሜ የመንገድ** ፕሮጀክቶች፤

**25.2** **በማቻከል ወረዳ** የአማኑኤል - በለምና ፕሮጀክት 1.20 ኪ.ሜ ላይ ያልተጠናቀቀ አነስተኛ ድልድይ በመኖሩ በመኪና ማለፍ የማይቻልና አገልግሎት መስጠት የማይችል ከመሆኑ በተጨማሪ እስከ 1.20 ኪ.ሜ ድረስ ያለው መንገድ በሳር የተሸፈነ በመሆኑ መንገዱን ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ መሆኑ፤

**25.3** **በእነብሴ ሳር ምድር** በድምሩ ብር 23,457,190.29 ወጪ የተደረገባቸውና 28.587 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው 3 ፕሮጀክቶች (በ2004 በጀት ዓመት የተገነባው **የመርጦ ለማርያም-ቀንዳች** ፕሮጀክት እንዲሁም በ2005 በጀት ዓመት የተገነቡት **የመርጦ ለማርያም - አንሳ** እና **የደርጅ-እነጀምበር** ፕሮጀክቶች) ፤

25.4 **በጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ** በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመት የተገነቡ፣ በድምሩ ብር 3,288,323.15 ወጪ የተደረገባቸውና 17.34 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው **የእምባዎች ቁስቋም-ቶራ ሜዳ** እና **የቶራ ሜዳ- ትግዳር** ፕሮጀክቶች በበጋም ሆነ በክረምት ወራት አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

**ምዕራብ ጎጃም ዞን**

25.5 **በደጋ-ዳሞት** ወረዳ ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት 12/04/2010 ዓ.ም ድረስ በ2008 ዓ.ም የተገነባውና 7.10 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የዝቋላ-ዳሞት ጽዮን ፕሮጀክት፤

25.6 **በሰከላ ወረዳ** በድምሩ ብር 6,722,452.67 ወጪ የተደረገባቸውና ግንባታቸው በ2006 እና በ2007 ዓ.ም የተከናወነው 11.01 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የከበሳ- አቢወትጮራ እና 11.02 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የገሬልታ-አሊቦ ፕሮጀክቶች፤

25.7 **በወምበርማ ወረዳ** በድምሩ ብር 4,538,711.36 ወጪ የተደረገባቸውና ግንባታቸው በ2005 እና በ2006 ዓ.ም የተከናወነው 8.84 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የሽንዲ - በሊማ እና 4.00 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የወገዳድ-ማርወለድ ፕሮጀክቶች፤

25.8 **ደቡብ አቸፈር ወረዳ** በ2005 ዓ.ም በብር 11,705,514.10 የተገነባውና 21.12 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው **የኑኑ አቲባርኳ-አንከሻ ሙንገት** ፕሮጀክት፤

25.9 **በሰሜን አቸፈር ወረዳ** በ2005 ዓ.ም በብር 2,013,363.96 የተገነባውና 11.50 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የይስማላ-ሳምብላ ፕሮጀክት በጋ ከክረምት አገልግሎት የማይሰጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**ሰሜን ጎንደር ዞን**

25.10 **በቋራ** ወረዳ በድምሩ በብር 31,631,695.86 የተደረገበትና 42.36 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው 3 ፕሮጀክቶች (*በ2007 የተገነባው ነብስ ገበያ ቁጥር1-ቁጥር 4 ፕሮጀክት እንዲሁም በ2009 የተገነቡት መሃዲደ-በርሜል እና በርሜል-ደዛጎመዛ ፕሮጀክቶች)* ፤

25.11 **በምስራቅ በለሳ ወረዳ** በ2008 ዓ.ም በብር 4,898,414.49 ወጪ የተገነቡትና 24.6 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸው የጣይመን-ጣርጣሯ እና የጎጋ-አቅጤ ፕሮጀክቶች፤

25.12 **በአለፋ ወረዳ** በተለያዩ በጀት ዓመታት የተገነቡ በድምሩ 48.96 ኪ.ሜ ርዝመት ያላቸውና የተከፈለባቸውን የገንዘብ መጠን ማስረጃ ማግኘት ያልተቻለባቸው 5 ፕሮጀክቶች *(በ2005 ዓ.ም አምቻሆ-እሰይ ደብር፣ በ2006 ዓ.ም አንከል -ጎሽቤተ 80፣ በ2008 ዓ.ም ከቤተ 80- ዘከር፣ በ2009 ዓ.ም ከዘከር-ጋራስጌ እና በ2009 ዓ./ም ከአጸደማርያም-ቸባ ፕሮጀክቶች)* በበጋም ሆነ በክረምት ወራት አገልግሎት የማይሰጡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ለዚህም መንገዱን ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ በተለያዩ ምክንያቶች የመሬት ቆረጣና የስትራክቸር፤ የውሃ መፋሰሻ ስራዎች ወዘተ የማጠናቀቂያ ስራዎች ባለመሠራታቸው እና ከየፕሮጀክቶቹ ክፍሎች የተወሰኑ ስራዎች ባለመጠናቀቃቸውና አንዳንዶቹም የተቋረጡ መሆናቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም መንገድ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ዋና ሞተር መሆኑን ተገንዝበን አገልግሎቱ እንዳይሟላ ምክንያት የሆኑትን ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች፤ የስትራክቸር ስራዎችና በመንገዶች መካከል ያልተሰሩ

የድልድይ ግንባታዎችን በእቅድና በፕሮግራም በማካተት ማህበረሱንና የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ በማሰተፍና በበጀት በማስደገፍ መንገዶቹ የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ፤የማህበረሰቡን የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲያቃልሉ ብሎም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስተጋብር እንዲያሳልጡና ሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎችን እንዲግዙ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል፡፡

**ተቋራጭ እና አማካሪ ማህበራት ብድርና የሊዝ አመላለስን በተመለከተ፤**

በሁሉን አቀፍ የወረዳ ገጠር መንገድ ፕሮግራም ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 86/2003 አንቀጽ-11 እና ለአንድ መንገድ መስሪያ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በድጋሜ በሚደረጉ ተከታታይ ክፍያዎች ላይ እየተቀነሰ የመጨረሻ ክፍያ ሲደረግ ሁሉም ቅድሚያ ክፍያ ተቀንሶ ማለቅ እንዳለበት የፋይናንስ መመሪያው ያስገድዳል፡፡

በዚህ መነሻነት በሁሉን አቀፍ የወረዳ ገጠር መንገድ ፕሮግራም አገልግሎት ስር በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩ አማካሪና ተቋራጭ ማህበራት በሊዝ፣በብድር እና በቅድሚያ ክፍያ የወሰዱትን ገንዘብ ከላይ በተገለፁት መመሪያዎች መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

26. **የአማካሪ ማህበራት ብድርና አላግባብ ክፍያን በተመለከተ፤**

26.1 **በሁለት እጁ እነሴ** ወረዳ በ2004 ዓ.ም በብድር ከወረዳው ለYWC የተሰጠው ብር 600,000.00 ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.2 **በጎንጅ ቆለላ** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው 10 ፒላርስ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2008 በጀት ዓመት የወሰደው ብድር ብር 600,000.00 ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.3 **በሰከላ** ወረዳ አባይ ምንጭ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2004 በጀት ዓመት አለአግባብ ከተከፈለ ክፍያ ብር 1,281,720.593 ውስጥ ብር 839,396.65 (65.49%) በ2005 በጀት ዓመት ተመልሷል ቢባልም በማስረጃ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

26.4 **በቡሬ** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው ፈጣም የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2009 በጀት ዓመት የተሰጠ ብድር ብር 600,000.00 በፍርድ ቤት እግድ ምክንያት ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.5 **በቋሪት** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው ካራቫን የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከወረዳ በጀት ብድር 46,902.44 ያልተመለሰ ሲሆን ማህበሩም ስራ ያቋረጠ መሆኑ፤

26.6 **በወንበርማ** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው አንድነት የገጠር መንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከወረዳ በጀት ብድር የወሰደው ብር 21,262.60 ማህበሩ ስራ ያቋረጠና ብድሩም ያልተመለሰ መሆኑ፤

**ሜጫ ወረዳ**

26.7 ንብ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከ2007 በጀት ዓመት በፊት የወሰደው ብድር ብር 1,250,000.00 እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት የተሰጠው ብድር ብር 256,000.00 በድምሩ ብር 1,506,000.00 ያልተመለሰ መሆኑ፤

**በደቡብ አቸፈር ወረዳ**

26.8 ለዞብል የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2006 በጀት ዓመት የተሰጠ ብድር ብር 500,000.00 ያልተመለሰና ማህበሩም ስራ ያቋረጠ ሲሆን በ2010 ተመልሷል ቢባልም ማስረጃ አለመቅረቡ፤

26.9 ብሩህ ተስፋ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2009 በጀት ዓመት የወሰደው ብድር ብር 450,000.00 ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.10 **በጃቢ ጠናን ወረዳ** ሐመር የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2007 በጀት ዓመት የወሰደው ብድር ብር 108,638.48 ከ3 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ቢረጋገጥም ማህበሩ እዳ የለበትም ከማለት ያለፈ ማረጋገጫ በምላሹ አለመቅረቡ፤

**ሰሜን ጎንደር ዞን**

26.11 **በደባርቅ** ወረዳ ለማሪሰግ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2008 ዓ.ም በብድር የተሰጠ ብር 700,000.00 ከ2 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.12 **በወገራ** ወረዳ ለማሪሰግ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2009 ዓ.ም በብድር የተሰጠ ብር 100,000.00 ከ1 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.13 **በምስራቅ በለሳ** ወረዳ ለኃይለ አብ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2009 ዓ.ም በብድር ከተሰጠው ብር 800,000 ውስጥ ብር 500,000 ከ1 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

26.14 **በታች አርማጭሆ** ወረዳ ለኤግል የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2004 ዓ.ም በብድር የተሰጠ ብር 1,162,000.00 ከ6 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

**ጭልጋ ወረዳ**

26.15 ለመክሊት የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከ2004 እስከ 2009 ዓ.ም በብድር ከተሰጠው በድምሩ ብር 8,389,491.09 ውስጥ ብር 5,171,918.48 እንዲሁም ለአባይ ግድብ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከ2004-2009 ዓ.ም በብድር ከተሰጠው ብር 12,194,455.00 ውስጥ ብር 1,310,271.39 ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ወቅት በማስረጃ ቢረጋገጥም ኦዲት ተደራጊው ቢሮ በቅደም ተከተል በምላሹ እዳው ብር 772,856.22 እና ብር 103,096.75 ብቻ እንደቀራቸው ስለተገለጸ ወደፊት በክትትል ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ መሆኑ፤

*በድምሩ ብር **15,625,224.64 በብድር** መልክ አላግባብ ተከፍሎ ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል።*

## 27. የአማካሪ ማህበራት የሊዝና ቅድመ ክፍያ አመላለስን በተመለከተ፤

**ምስራቅ ጎጃም ዞን**

27.1 **በደባይ ጥላት ግን** ወረዳ የዩራፕ ፕሮጀክቶችን ይሰራ የነበረው ድብዛ የተባለው የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2004 ዓ.ም ከወሰደው የመሳሪያ ሊዝ ብር 2,747,396.47 ውስጥ ብር 82,383.64 (3%) የመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 2,665,012.83 (97%) ተጠቃሎ መመለስ ከነበረበት ከ2 ዓመት በላይ የዘገየና ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ወቅት ቢገኝም በምላሹ ላይ ቀሪ እዳው ብር 731,250.40 ብቻ መሆኑ በመገለጹ ለውጡ ወደፊት በክትትል ኦዲት የሚረጋገጥ መሆኑ፤

27.2 **በማቻከል** ወረዳ የዩራፕ ፕሮጀክቶችን ይሰራ የነበረው ጺዮን የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2004 ዓ.ም ከወሰደው የመሳሪያ ሊዝ ብር 2,747,396.47 ውስጥ ብር 2,479,586.11 (90.25%) የመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 351,869.84 ማህበሩ የተበተነ ስለሆነ መመለስ ከነበረበት ከ2 ዓመት በላይ የዘገየና ያልመለሰ መሆኑ፤

27.3 **በሁለት እጁ እነሴ** ወረዳ በ2004 ዓ.ም ከመሳሪያ ሊዝ ብር 94,800.00፣ ከቅድሚያ ክፍያ ብር 910,000.00 በድምሩ ብር 1,004,800.00 ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ወቅት በማስረጃ ቢረጋገጥም ቀሪ እዳው ብር 910,000.00 ብቻ መሆኑ በምላሹ ስለተገለጸ ወደፊት በክትትል ኦዲት የሚረጋገጥ መሆኑ፤

**ምዕራብ ጎጃም ዞን**

27.4 **በጎንጅ ቆለላ** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው *10* ፒላርስ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2008 እና በ2009 ከተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 1,199,335.35 ውስጥ ብር 906,199.43(75.56%) የተመለሰ ሲሆን ብር 293,135.92 (24.44%) ያልተመለሰ መሆኑ፤

27.5 **በሰከላ** ወረዳ አባይ ምንጭ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከ2004-2009 በጀት ዓመት ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ብር 8,405,687.46 ውስጥ ብር 6,740,641.63(80.19%) የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 1,665,045.83 (19.81%) ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ቢረጋገጥም በኦዲት መልስ ቀሪ እዳው ብር 52,923.59 ብቻ እንደሆነ ቢገለጽም ለውጡ በቀጥይ በክትትል ኦዲት የሚረጋገጥ መሆኑ፤

27.6 **በቋሪት** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው ካራቫን የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2007 በጀት ዓመት ከተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 850,000.00 ውስጥ ብር 434,831.01 ያልተመለሰ ሲሆን ማህበሩም ስራ ያቋረጠ መሆኑ፤

27.7 **በሰሜን አቸፈር** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው ሳምኬት የገጠር መንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከሊዝ ብር 2,745,359.90 እና ከዩራፕ በጀት ቅድሚያ ክፍያ የወሰደው ብር 1,880,993.33 በድምሩ ብር 4,626,353.30 ውስጥ ብር 2,604,811.29 ያልተመለሰ ሲሆን ማህበሩ ስራ ያቋረጠና የማህበሩ ገልባጭ መኪና የገቢዎች ባለስልጣን የተወሰደው ሲሆን በምላሹ እንደተገለጸው ከወረዳው ያለባቸው እዳ መመለሱ ቢጠቀስም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤

27.8 **በወንበርማ** ወረዳ በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከሚሰራው አንድነት የገጠር መንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከሊዝ ብር 3,525,937.27 ውስጥ ብር

610,184.56 ማህበሩ ስራ ያቋረጠና ያልተመለሰ መሆኑ፤

27.9 **ሜጫ ወረዳ** አንተናኔ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2007 በጀት ዓመት ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ብር 850,000.00 እና ከሊዝ ብር 2126.62 (2,745,359.97-2,743,233.35) በድምሩ ብር 852,126.62 ያልተመለሰ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ቢረጋገጥም በምላሹ እዳ የለባቸውም ከማለት ያለፈ ማስረጃ አለመኖሩ፤

27.10 **በደቡብ አቸፈር ወረዳ** ዞብል የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በሊዝ ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ ብር 286,095.88 (2,745,359.97-2,459,264.09)፤ በ2006 በጀት ዓመት ከተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 123,807.51 ውስጥ ብር 407,986.91 ያልተመለሰ ሲሆን ማህበሩም ስራ ያቋረጠ መሆኑ፤

27.11 **በጃቢ ጠናን** ወረዳ ፍኖተ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2009 በጀት ዓመት በቅድሚያ ክፍያ ከወሰደው ገንዘብ ብር 869,556.00 ከ1 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

**ሰሜን ጎንደር ዞን**

27.12 **በደባርቅ** ወረዳ ለአይቤክስ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2008 ዓ.ም በቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው ብር 850,000 ውስጥ ብር 138,049.26 (16.24%) ከ2 ዓመት በላይ ያልተመለሰ መሆኑ፤

27.13 **በጃናሞራ** ወረዳ ቀስተ ደመና የገጠር መንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር 4.5 ኪ.ሜ ርዝመት ያለዉን የቧሂት ዋና መንገድ-ድበበ (ቃይት) ፕሮጀክት ለመስራት በ2008 በጀት ዓመት ዉል ወስደዉና ቅድሚያ ክፍያ ብር 81,000.00 ተከፍሏቸው ከ2 ዓመት በላይ ስራው ያልተጀመረ/ ገንዘቡ ያልተመለሰ መሆኑ፤

27.14 **ጭልጋ ወረዳ** ለመክሊት የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር ከ2004-2006 ዓ.ም በሊዝ ከተሰጠው በድምሩ ብር 4,117,077.24 ውስጥ ብር 1,387,260.10፣ በ2004 ፣በ2005 ፣በ2007 እና በ2008 ዓ.ም በቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው በድምሩ ብር 2,238,416.72 ውስጥ ብር 1,159,129.33፣ ጠቅላላ በድምሩ ብር 2,546,389.43 ያልተመለሰ መሆኑ፤

**ደምብያ ወረዳ**

27.15 ለንጋት የመንገድ ስራ ተቋራጭ ማህበር በ2007 ዓ.ም በቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው ብር 1,360,000 ውስጥ ብር 617,429.38 ያልተመለሰ መሆኑ፤

27.16 ለጃንተከል አማካሪ ማህበር በ2004 ዓ.ም በቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው ብር 70,000.00 ውስጥ ብር 40,833.31 የተመለሰ እና ብር 29,166.69 ያልተመለሰ መሆኑ፤

በናሙና ከታዩት ስራዎች በድምሩ ብር **19,896,276.53** ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ 24/04/2010 ዓ.ም ድረስ ያልተመለሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ለዚህም ኦዲት ተደራጊው የመንገድና ትርንስፖርት ቢሮ ለኦዲት ግኝቶች በሰጠው ምላሽ ባሁኑ ጊዜ ያለው ያልተመለሰ ብድር ብር 9,656,161.75 ብቻ መሆኑን ገልጾ የመንግስት ገንዘብ በየጊዜው እየተመለሰ መሆኑን፤የተወሰኑ ማህበራት የሊዝ ዕዳቸውን ከፍለው መጨረሳቸውን፣ ሌሎች ደግሞ ዕዳቸውን ለማስመለስ በክትትልና በሂደት ላይ መሆኑን የገለጸ ሲሆን የዚህ ምላሽ ትክክለኛነት ሙሉ በሙሉ የሚረጋገጠው በቀጣይ **በሚደረግ የክዋኔ የክትትል ኦዲት** ወቅት መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

**የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

## V. የአደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም አፈጻጸም የተጠቃሚ ልየታን በተመለከተ፡-

27. **የተጠቃሚ ልየታ ሥራዎች አሳታፊ፣ መረጃን መሰረት ባደረጉና ፍትሃዊነትን በተከተሉ አሠራሮች መፈጸም አለበት ይሁን እንጂ ከዚህ መስፈርት ጋር ተያይዞ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተዉለዋል፡፡**

**በደቡብ ጎንደር ዞን አዳጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

27.1 በላይ ጋይንት ወረዳ በተሰጠ የኦዲት መጠይቅ ላይ እንደተገለፀዉ የተጠቃሚ ልየታ ስራዎች መረጃን መሰረት ያላደረገና ማህበረሰቡን ያሳተፈ አለመሆኑ፤

27.2 በአንዳንድ ወረዳዎች ሆን ተብሎ ( በላይ ጋይንት ወረዳ እያያ ምህረት እና ዜና ምህረት የተባሉትን) የቁስ ምህረት ቤተሰብ አስመስሎ በቀበሌው የሌሉ የሰው ስም በመሰየም እርዳታን መጠቀም መኖሩ፣

27.3 ትክክለኛ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸውን በወቅቱ ለይቶ ተጠቃሚ አለማድረግ፣ በልየታ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችን ለይቶ በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት፤መካተት የማይገባቸውን ሰዎች ተቆራርጦ ከፕሮግራሙ አለማስወጣት የታዩ ችግሮች መሆናቸው፣

27.4 የዞን ቅሬታ ሰሚ በታች ጋይንት ወረዳ በ15 ቀበሌዎች በተካሄደ ስብሰባ ከተነሱ የምዝገባ /የልየታ/ ችግሮች ውስጥ፤ በአድሎ መመዝገብ ፤ድሃዎችን ሳይመዘግቡ መቅረት፤ በሌሉ ሰዎች መመዝገብ፣ በሞቱ ሰዎች መጠቀም፤ አመራሩ ለራሱ ዘመድ/ልጅ ተጠቃሚ ማድረግ የተባሉ መሰረታዊ ችግሮችን ያሳወቀ ቢሆንም ተጠሪ ጽ/ቤቱ የተጠቀሱትን መነሻ በማድረግ የወሰደው የማጣራት እርምጃ አለመኖሩ፣

27.5 በላይ ጋይንት ወረዳ፡- በቀበሌ 03 በፕሮግራሙ የማህበረሰብ ልማት ተጠቃሚ የሆኑት አንድ በግብርና የሚተዳደሩ ባለ 80 ዓመት እናት ከእሳቸው ጋር በ4 ቤተሰብ ከልጆቻቸው ጋር የተመዘገቡና የልጆቻቸው ዕድሜ ከ12-18 ዓመት ሲሆን በ80 አመት እድሜ ያሉ ሴቶች መውለድ በማይቻልበት ሁኔታ ሶስቱም ልጆቻቸው እንደሆኑ ተደርጎ የተገኘ መሆኑ፣

**በሰሜን ወሎ ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

- በተጠሪ ጽ/ቤቱ በ2008 በጀት አመት ከልየታ ጋር በተያያዘ የቀበሌ አመራሩ ራሱንና ቤተሰቡን በተጠቃሚነት መመዝገብና ፍትሃዊነቱን ማዛባት፤መካተት የሚገባዉን የድሃ ድሃ ህዝብ እያለ የተሻለ ገቢ ያላቸዉን ግለሰቦች በፕሮግራሙ ማካተት፤በሌሉ ሰዎች ስም መጠቀም፤ ለምሳሌ
  - ❖ በዋድላ ወረዳ በ2009 በጀት አመት በቀበሌ 09 የዋና አስተዳዳሪው 3 ልጆች ያላአግባብ በሚስቱ አባት

ስም ቤተሰብ በማስመሰል አስገብቶ መጠቀም፣ የወረዳው አስተዳደር ጸጥታ ሃላፊ 4 ልጆች እና የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ 2 ልጆች በተረጂነት ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ፣

- በመቄት ወረዳ ሃሙሲት ቀበሌ ስማቸዉ በማስተር ሊስት ላይ የተመዘገበ (ያለ) ነገር ግን በቀበሌዉ የሌሉና የማይታወቁ 9 ሰዎች በስማቸዉ ክፍያ ሲከፈልበት የቆየ መሆኑን ተጠሪ ጽ/ቤቱ የገለጸ ቢሆንም ደብዳቤው ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ችግሩን ያጣራበትና የተወሰደው እርምጃ አለመኖሩ፣
- የመንግስት ሰራተኛ የሆኑና ወፍጮ ያላቸዉ ግለሰቦችን በፕሮግራሙ እንዲካተቱ የተደረገ መሆኑ፣

**በ2009 በጀት አመት በላስታ ወረዳ ከልየታ ጋር በተያያዘ የታዩ ችግሮች፡-**

- *አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል ከ2006----2008 ዓ.ም በቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ለተከታታይ 3 ዓመት ሲጠቀም መቆየቱ፣*
- በእንጃፋት (ቀበሌ 017) የሚኖር አንድ ፎርማን ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተስፋ ቢረዳ በተባለ የሃሰት ስም በ3 ቤተሰብ ለ6 ወር ሲጠቀምበት መቆየቱንና ወጣት ባለቤቱን እሙሀይ ብሎ በመሰየም እና በ3 ቤተሰብ በማድረግ ከማህበረስብ ወደ ቀጥተኛ ተረጅ በማምጣት 1 ዓመት ያላግባብ ሲጠቀም መቆየቱ፣
- የወረዳው የግብርና ጽ/ቤት የጥበቃ ሰራተኛ የሆነ አንድ ግለሰብ በራሱ በ5 ቤተሰብ እና በሚስቱ በ5 ቤተሰብ በጠቅላላ በ10 ቤተሰብ ከ2008 ዓመት ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያላግባብ ሲጠቀሙ መቆታቸው፣
- በ08 (ገለሶት)ቀበሌ አንድ የቀበሌ አመራር ልጅ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ለተከታታይ 7 ወራት በድጋሜ በስሙ ሲረዳ የቆየ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፣

**የፕሮግራሙን ተጠቃሚዎች ወቅታዊ ሁኔታዎችና ለውጦች የማረጋገጥና ምዝገባ የማስተካከል ሥራዎች በየዓመቱ መከናወንን በተመለከተ፡-**

**28.** የፕሮግራሙን ተጠቃሚዎች ወቅታዊ ሁኔታዎችና ለውጦች የማረጋገጥ እና ምዝገባ የማስተካከል [በአካባቢው ስለመኖራቸው፤ የቤተሰብ ቁጥር ለውጦች፤ የተጠቃሚነት ዓይነት ለውጥ፣...ወዘተ] ሥራዎች በየዓመቱ መከናወን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከተሉት ግኝቶች ተስተዉለዋል፡፡

**በደቡብ ጎንደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

28.1 በታች ጋይንት ወረዳ በቀበሌ 09 ከሞተ 8 አመት የሆነው አንድ ግለሰብ በሁለት ቤተሰብ በመመዝገብ እና ሚች እንዳለ ተደርጎ እስከ 2008 በጀት አመት በስሙ ሲበላበት መቆየቱ፣

28.2 በ2009 በጀት አመት በላይ ጋይንት ወረዳ በቀበሌ 03 ከልየታ ጋር የታዩ ችግሮች፤

- አንድ ዘበኛ የነበሩ እና በህይወት የሌሉ ግለሰብ የቤተሰብ ብዛት 2 ገንዘቡን የሚወስዱት ቤተሰቦቻቸው ያልሆኑ ግለሰቦች መሆናቸው፣
- አንድ ግለሰብ የቤተሰብ ብዛት 5 የሆነ 4ቱ ቤተሰብ ስማቸው የማይታወቅ በሀገር የሌሉና በተመሳሳይ 1 ግለሰብ የቤተሰብ ብዛት 5 ሲሆኑ 4ቱ በሀገር የሌሉ መሆኑን በክትትሉ ወቅት የተረጋገጠ መሆኑ፣

**በሰሜን ወሎ ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

28.3 በ2009 በጀት አመት በላስታ ወረዳ በቀበሌ 017 (እንጃፋት):- ቋሚ ገቢ ያላቸው ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የድሃ-ድሃ የሆኑ አካላት መጠቀም የነበረባቸውን አላግባብ ሲጠቀሙ መቆየታቸው፤

- *አንድ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ወደ ሌላ ቀበሌ (ግራራይ) ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ሲዛወሩ ኮታውን ለሌላ ሰው በማከራየት ያላግባብ ለአንድ አመት ግለሰቦች እየተጠቀሙ መገኘታቸው፣*
- *በቀበሌ (02 ) ብልባላ የሚገኝ አንድ ተረጅ የመንግስት ስራ ከያዘ 2 ዓመት የሆነውን በእሱ ምትክ የደሃ ደሃ መተካካት ሲገባው በማህበረሰብ ልማት ስራ እንደሚሰራ በማድረግ ግለሰቦች ያለ አግባብ እየተጠቀሙበት መገኘቱ፤*
- *አንድ ግለሰብ ከ2006- 2008 ዓ.ም በቀበሌ 02 (ብልባላ ) መምህር ሁኖ ለተከታታይ ለ3 ዓመት ያላግባብ በማህበረሰብ ልማት ሲጠቀም መቆየቱ፤*
- *አንድ ግለሰብ ከ2007--2008 ዓ.ም በቀበሌ 02 (ብልባላ) መምህር ሆና ለተከታታይ ለ2 ዓመት ያላግባብ በቀጥታ ተረጅ ሆና ስትጠቀም መቆየቱ፤*
- *አንድ ግለሰብ ከ2006---2008 ዓመት በቀበሌ 02 (ብልባላ) የላሊበላ የመሰናዶ መምህር ለተከታታይ 3 ዓመት ያላግባብ ሲጠቀም መቆየቱ፣*
- *1 ግለሰብ በኢንጅነሪንግ ተመረቆ ስራ ከያዘ 2 ዓመት የሆነው የማህበረሰብ ልማት እየተጠቀመ መገኘቱ፣*
- *አንድ ግለሰብ የአብቁተ /የአክሲ/ ሰራተኛ የሆነ ለ3 ዓመት በሴፍትኔት ሲረዳ መቆየቱ፣ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ የሆነ ለ2 አመት ሲረዳ የነበረ መሆኑ፣*
- *አንድ የመከላከያ ሰራዊት ሆኖ ለ3 ዓመት ያላግባብ ኮታውን ሳያነሱ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ፣*

**30. ክፍያዎች ለተጠቃሚዎች በወቅቱ መድረስን በተመለከተ:-**

ክፍያዎች ለተጠቃሚዎች በወቅቱ [የማኅበረሰብ ልማት ሥራ ከተጠናቀቀበት ወር ጀምሮ ለገንዘብ ተጠቃሚዎች በ20 ቀናት፤ ለእህል ተጠቃሚዎች ደግሞ በ30 ቀናት ውስጥ] መፈጸም ይኖርበታል። ይሁን እንጂ በዚሁ ላይ በመነሳት በተደረገ ኦዲት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተውለዋል።

**በደቡብ ጎንደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

30.1 የሴፍቲኔት ክፍያዎች በሁሉም ወረዳዎች በታቀደላቸው ጊዜ /ወቅት/ ጠብቆ የማይሰራጩ/ የማይከፈሉ መሆኑ፣

30.2 በ2007 በጀት አመት በወረዳዎች ለተጠቃሚ የሚመጣውን በጀት በአግባቡ አለማሰራጨት፣ ቀበሌ ውስጥ በሌለ ተጠቃሚ ያለ አስመስሎ መጠቀም፣ ተጠቃሚ መሆን የማይገባውን ተጠቃሚ ማድረግ (አልፎ አልፎም መምህርና ፖሊስ ተጠቃሚ ሆኖ መገኘት) በሁሉም ወረዳና ቀበሌዎች የተስተዋሉ ችግሮች መሆናቸው፤

- ***በቀበሌ 19** አንዲት እናት የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከዚህ ዓለም ተለይተዋል በመባል የ2009 በጀት አመት ክፍያ ያልተከፈላቸው ሲሆን የኦዲት ቡድኑ በክፍያ ጣቢያው ተገኝቶ የተባለችውን ተጠቃሚ በአካል ክፍያ ይሰጠኝ በማለት ለከፋዮች (የተጠቃሚ መለያ ቁጥር 3-35-36-0-2‹53 በቀን 8/09/08 የተሰጣት ካርድ) በመያዝ ቅሬታ እያቀረቡ የተገኙ መሆኑ፣*

**በሰሜን ወሎ ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

30.3 በ2009 በጀት አመት ከመቄት ወረዳ ወደ ዋድላ ወረዳ ከተጠቃለሉ ከሁለቱ ቀበሌዎች የማጥራት ስራ ሲሰራ ከተገለጹት ከማህበረሰብ ልማት ተጠቃሚዎች ውስጥ

- 4 ተጠቃሚዎች ስማቸው በማስተር ሊስት ላይ እያለ ክፍያ የማይወስዱና የነዚህን ክፍያ (ብር እና እህል) ስማቸው በማስተር ሊስት የሌሉና እነሱ ሲጠሩ እነሱን በመምሰል ክፍያቸው የተወሰደባቸው መሆኑን መረጋገጡ፡፡
- በማህበረሰብ ልማት ተጠቃሚ የሆኑ 7 ስማቸው በማስተር ሊስት ላይ ያለ ሆኖ ሰዎቹ (ግለሰቦቹ) ግን በቀበሌው የሌሉ /የማይታወቁ/ እና የነሱን ክፍያ (የገንዘብና የእህል) አመራሩ እየተቀበለ ሲጠቀምበት የቆየ(የከረመ) መሆኑ፡፡
- በመቄት ወረዳ የመንግስት ሀብት ብር 70,739.00 እና እህል (ስንዴ እና ክክ) ያላግባብ የወጣ መሆኑ በመረጃ መረጋገጡ፣

**የማህበረሰብ ልማት ስራዎች አፈፃፀምን በተመለከተ፡-**

31. **የማኅበረሰብ ልማት ሥራዎች ሁሉንም ባሳተፉ ጥናቶች ሊለዩ፤ የተሟላ ዕቅድና የድርጊት መርሃግብር ተዘጋጅቶላቸው መፈጸም አለበት፡፡** ይሁን እንጂ በዚሁ ላይ በመነሳት በኦዲት ሲጣራ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተስተውሏል፡፡

**በደቡብ ጎንደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

31.1 በስማዳ ወረዳ በፈሳስ የወንዝ ጠለፋ መስኖ ስራ በአካል ምልከታ ወቅት የተስተዋሉ ሁኔታዎች፡-

- *ስራው የተጀመረው በ2008 መጋቢት ወር ላይ ሲሆን የተያዘለት በጀት ብር 812,743.32 ሆኖ በ2008 እና 2009 ዓ/ም ለመስኖ ግንባታው የወጣ ወጪ ብር 1,306,949.51 /ተጨማሪ ወጭ ብር 494,206.19፣/ የማልማት አቅም 20 ሄክታር መሬትና ለ312 አርሶ አደር ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን የወረዳው የሴፍቲኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ስራዎች የኢንፍራስትራክቸር ባለሙያ በቀን 11/01/2010 በተጻፈ ደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም በአካል ሲታይ የተገኙ ሁኔታዎች ደግሞ፡-*
- የመስኖው ውሀ መውረጃ የካናል ስራዉ በጎርፍ የተሰበረ፣ የተሰነጣጠቀና የፈራረሰ፣ በደለል የተሞላ፣ የካናሉ ጎንና ጎኑ እኩል ስፋት የሌለው፣ የውሀው መውረጃ ወለሉ በርዝመቱ ልክ ሙሉ በሙሉ በስሚንቶ ያልተሰራ /ያለበሰ/ መሆኑ፤
- ወደ አርሶ አደሩ መሬቶች የውሀ ማፋሰሻ ተብለው የተሰሩ የዉሃ ማሳለፊያዎች ሁሉም ሙሉ በሙሉ በሜታል ሺት ያልተዘጉ በመሆኑ የ2009 ክረምት ከካናሉ የሚወጣው የጎርፍ ውሀ በ7 አርሶ አደሮች መሬት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
- ወደ ፈሳስ ወንዝ የሚገባ ገባር ወንዝ (ጎድንዲት ወንዝ) በመኖሩ ካናሉ የተሰበረ መሆኑ፣ የጎርፍ መቀልበሻ ያልተሰራለት በመሆኑ የመስኖ ካናሉ በጎርፍ የፈረሰ መሆኑ፤

- በ2008 በጀት አመት በመስኖው የሰብል ምርት ትጠቀማላችሁ ተብለው ምርጥ ዘር ገዝተው ስራው ባለመጠናቀቁ የዘር ግዥ የፈጸሙት አርሶ አደር ኪሳራ ያደረሰና ለ312 አርሶ አደሮች ጥቅም ይሰጣል ቢባልም እስከ ኦዲቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ጥቅም ሳይሰጥና ስራውም ሳይጠናቀቅ መገኘቱ፣

31.2 በቀድሞው በግዳን ወረዳ በ011 ቀበሌ /በአዲሱ በአንጎት ወረዳ/ ልዩ ስሙ ቀበሮ ሜዳ ህዳሴ ግዳን የሚል ስያሜ የተሰጠው በ2007 ዓ/ም የተሰራው ግድብ በአካል ሲታይ የተገኙ ሁኔታዎች፡-

- ግድቡ በ2007 በጀት አመት ተሰርቶ የተጠናቀቀና በውሀ ከሞላ በኂላ ለመስኖ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ የተዘጋጀ ቢሆንም በአካል እስከታየበት ቀን ድረስ የመስኖ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
- የተሰራው ግድብ በስሩ ውሀ የሚያፈስ መሆኑ፣
- ግድቡ ላይ የተገጠሙ የውሀ ማፋሰሻ የብረት ቧንቧዎች በግድቡ የተጠራቀመውን ውሀ ወደ አርሶ አደሩ ያስተላልፋሉ ተብለው የተዘጋጁ ቢሆንም የተጠራቀመው የውሀው ከፍታ ቧንቧዎች ከተገጠሙበት ከፍታ ድረስ የማይደርስ በመሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣
- ከግድቡ ወደ አርሶ አደሩ ውሀውን ተቀብሎ ይወስዳሉ ተብለው የተዘጋጁ የውሀ ቧንቧዎች (ቱቦዎች) ያልተገጣጠሙና ተነጣጥለው በአርሶ አደሩ መሬት ላይ በተበታተነ ሁኔታና ለብክነት በተጋለጠ መልክ ተቀምጠው ያለአገልግሎት የተገኙ መሆኑ፣
- ግድቡ በክረምት ወቅት ከአቅሙ በላይ ውሀ አቁሮ በመያዝና በግድቡ ላይ የተገጠሙት ቧንቧዎች (ቱቦዎች) ያልታሸጉ በመሆኑ በቧንቧዎች (በቱቦዎች) ቀዳዳ የሚወጣውና ከግድቡ አቅም በላይ የሚፈሰው ውሀ በአርሶ አደር መሬት ላይ የጎርፍ /የአፈር መሸርሸር ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ፡፡

**የማኅበረሰብ ልማት ሥራዎች የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ መዋልን በተመለከተ፡-**

32. የማኅበረሰብ ልማት ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ተስተውለዋል፡፡

**በሰሜን ወሎ እና በደቡብ ጎንደር ዞን አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት፤**

32.1 በራያ ቆቦ ወረዳ፡-

- በ07 እና 011 ቀበሌዎች ላይ የካፒታል ፕሮጀክት ለመስራት ውል የወሰደው ረምሀይ ጠቅላላ ውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ስራውን ለመስራት ለ07 ቀበሌ ለሚሰራው የቅድሚያ ክፍያ ብር 97,468.25 እና ከ011 ቀበሌ ላይ ከሚሰራው ብር 135,757.55 በመውሰድ ስራውን በመስራት ላይ እንዳለ አቋርጦ ሳያጠናቅቅ በመጥፋቱ ከሁለቱም ከወሰደው በድምሩ ብር 117,320.86 ተመላሽ እንዲያደርግ የራያ ቆቦ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ጽ/ቤት በቀን 30/10/08 በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም ገንዘቡ እስከ ኦዲቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ከ2 ዓመት በላይ ተመላሽ እንዳልሆነ የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት በሰጠው መረጃ መረጋገጡ፡

- በ011 ቀበሌ የሚገነባው የመስኖ ካናል ስራው በ19/10/2008 እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም ለኦዲቱ እስከተደረሰበት 30/4/2010 አለመጠናቀቁ፣
- ካናሉ በአካል ሲታይ የሚከተሉት ሁኔታዎች የተስተዋሉ መሆኑ፤
  - ✓ የአናት ስራው ያልተሰራ፤የካናሉ የውሀው መግቢያ በሩ በሜታል ሽት ያልተዘጋ መሆኑ፣
  - ✓ ለሰውና ለእንስሳት መሸጋገሪያ መንገድ ተብሎ የተሰሩ በካናሉ ላይ አለመገጠሙ፣
  - ✓ ለካናሉ ስራ ተብሎ በ2008 የቀረበ 210 ኩንታል ስሚንቶ ከጥቅም ውጭ መሆኑ እና በተጨማሪም፣ ወጭ የወጣባቸው ጠጠር፣ፌሮ ብረቶችና ለመወጠሪያ ተብለው የቀረቡ ጣውላዎች በየቦታው የወዳደቁ፣ ለፀሀይና ለዝገት እንዲሁም ለምዝበራ የተጋለጡ ሁነው መገኘታቸው፡፡

- በቀበሌ 07 እና በቀበሌ 028 የመስኖ ካናሎች የተሰሩ ቢሆንም ካናሎች በአካል ሲታይ ከላይ የተገለጹት ሁኔታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

32.2 በ2008 በጀት አመት በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት ከተሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች ውስጥ በሀብሩ ወረዳ በ021 ቀበሌ (ውላውላ) ወንዝ ላይ 350 ሜትር የመስኖ ካናል ስራ ለመስራት በእቅድ ከተያዘው ውስጥ 42 ሜትሩ ያለጥናት የተሰራ መሆኑን ስራው በ1/07/08 እንደተጀመረና ብር 488,577.60 ወጪ የወሰደ፣25 ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት በአመት ለ2 ጊዜ ለ74 አርሶ አደር ጥቅም የሚሰጥ እንደሆነ ቢገለጽም ስራው በባለሙያ ባለመጠናቱ ውሀው ይወጣል ተብሎ ከታሰበበት ቦታ ባለመውጣቱ የታሰበውን አገልግሎት መስጠት እንዳልተቻለ ታውቋል፡፡

- ግንባታው በአካል ሲታይ የተስተዋሉ ሁኔታዎች፡-
  - ✓ ወደ ካናሉ ውሀውን የሚያስገባው በሩ ባለመዘጋቱ በካናሉ በክረምቱ የገባው የወንዙ ውሀና ጎርፍ በአርሶ አደሮች መሬት ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ፣
  - ✓ ለካናሉ የጎርፍ መከላከያ ባለመኖሩ ካናሉ በደለልና በድንጋይ የተዘጋ መሆኑ፣
  - ✓ ካናሉ ሲሰራ መነሳትና መቆረጥ የነበረበት ዛፍ ሳይቆረጥ ከካናሉ ጋር አብሮ የተሰራ በመሆኑ በዛፉ ስርንቻ ካናሉ የተሰነጠቀ መሆኑ፣
  - ✓ ካናሉ በእንስሳት እግር፣በጎርፍ እና በወንዙ የክረምቱ ውሀ ሙላት ሀይል የተሰባበረ መሆኑ፣
  - ✓ የአናት ስራውን ደለል፣አሸዋ እና የወንዝ ውሀው ሙላት ባመጣው ድንጋይ የተጫነው /የደለለበት/ በመሆኑ በአካል ይኑር አይኑር በአይን ለማየት ያልተቻለበት ሁኔታ መኖሩ፣

32.3 በጉባላፍቶ ወረዳ በሴፍቲኔት ካፒታል በጀት በ2009 በጀት ዓመት ከተሰሩት መሰረተ ልማቶች ውስጥ በቀበሌ 013፣14 እና 017 የተሰሩትን በተመለከተ ሙሉ ስራው ጥናት ያልተደረገለት፣ እቅድ የሌለው መሆኑን ከወረዳው በተገኘ መረጃ የታወቀ ሲሆን በ013 እና በ014 ቀበሌወች በጋራ የሚጠቀሙበት የመስኖ ካናልን በተመለከተ ብር 1,569,840.93 ወጪ የተደረገበት፣ 456 አርሶ አደሮች በአመት ለ3 ጊዜ የመስኖ ሰብል ለማምረት ጥቅም የሚሰጥ እና ስራው በ2009 ጥር ላይ የተጀመረ ቢሆንም በአካል ሲታይ በስራው በርካታ የጥራትና የአሰራር ችግሮች የታየበት መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

**ለተጠቃሚዎች የሚሰጥ ብድር የመመለሻ ጊዜውን ጠብቆ እየተመለሰና ለተዘዋዋሪ ብድር መዋሉን በተመለከተ፡-**

33. በየጊዜው ለተጠቃሚዎች የሚሰጥ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ብድር የመመለሻ ጊዜውን ጠብቆ ሙሉ በሙሉ እየተመለሰ ለተዘዋዋሪ ብድር አገልግሎት እንዲውል መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲት ሲጣራ የሚከተሉት ተስተውለዋል፡፡

33.1 በክልል ደረጃ ከ2003–2006 በጀት አመት ከተሰራጨ ብድር ለማስመለስ የተያዘው እቅድ ብር **598,176,879.00** ሲሆን የተመለሰ ብር **285,562,830.00** (47.7%) ብቻ መሆኑ፣

33.2 በ2006 በጀት አመት በእብናት ወረዳ የብድር አመላለስን አስመልክቶ በማህበራት በኩል መመለስ ያለበት ከብር 21,146,359.32 ውስጥ የተመለሰ ብር 843,946.65 /3.9%/ ብቻ ሲሆን በአብቁተ ለማስመለስ ከታቀደው ከብር 9,013,452.17 ውስጥ የተመለሰ ብር 8,478,910 /94%/ መሆኑ እና ቀሪው ብር 534,542.17 አለመመለሱን፤

33.3 በዋድላ ወረዳ የፌዴራል ምግብ ዋስትና ብድር ከ1991---2002 ዓ.ም የተሰራጨና ያልተመለሰ ብር 7,527,627.72 የሚገኝ መሆኑ፤ ከዋድላ ወረዳ ወደ ጋዞ ወረዳ የተጠቃለሉ የሄዱ የ8 ቀበሌዎች ብድር ብር 2,491,344.30 ያልተመለሰ መሆኑ፣

**33.4** ለግዳን ወረዳ በተሰጠ የኦዲት መጠይቅ ላይ እንደተገለፀዉ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች የብድር አመላለስን በተመለከተ በወረዳዉ ከተሰጠዉ ብድር ከ21 ሚሊዮን ብር በላይ በወቅቱ አለመመለሱ፤ **በሰሜን ወሎ ዞን አዳጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ተጠሪ ጽ/ቤት**

33.5 የግዳን ወረዳ በ2009 በጀት አመት የብድር አመላለስን አስመልክቶ በበጀት ዓመቱ በአብቁተ ብር 4,000,000.00 እና በማኅበራት ብር 2,000,000.00 ለማስመለስ በዕቅድ ከተያዘዉ በድምሩ ብር 6,000,000.00 ዉስጥ በበጀት ዓመቱ የተመለሰ አለመኖሩ፣

33.6 ተጠሪ ጽ/ቤቱ በ2007 በጀት አመት ብድር አመላለስን አስመልክቶ እንደተገለጸው ከታቀደው ብር 78,236,639.9 ውስጥ የተመለሰ ብር 24,872,784.78 /32%/ ብቻ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

## VI. በጤና ጥበቃ ቢሮና በስሩ በሚገኙ ተቋማት የህክምና መሳሪዎች፣ መድሃኒቶች፣ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች አቅርቦት፣አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ በተመለከተ፣

### 34. የህክምና መሳሪያዎች ግዥ ሲፈፀም ከነሙሉ መለዋወጫቸው ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ

**ጤና ጥበቃ ቢሮ**

34.1 በፈረስ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ከሦስት አመት በፊት ገቢ የተደረገ አንድ አዲስ የቀዶ ጥገና መስሪያ አንስቲዣን መስጫ ማሽን ሲመጣ ሞኒተር ከመሳሪያው ጋር አብሮ አለመምጣቱ፡፡

34.2 ለንደን ከሚገኘው ኢምፔሪያል ኮሌጅ በ2006 ዓ.ም ለክልሉ ሪጅናል ላብራቶሪ በስጦታ የተሰጠ አንድ አልተራ ሳውንድ ከኬንያ ናይሮቢ የራጅ አቅራቢ ድርጅት በኮሌጁ በኩል ተገዝቶ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ አንድ ባለሙያ አልትራ ሳውንዱን እስከ መለዋወጫው /Accssories/ እንዲያመጣ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተልኮ አልተራ ሳውንዱን ብቻ አምጥቶ ገቢ ሲያደርግ የአልትራ ሳውንዱ መለዋወጫ በድምሩ ብር 106,041.00 ($ 3,900.00) የሚያወጣ ዕቃ ገቢ ባለመደረጉ መሳሪያው በሪጅናል ላቦራቶሪው ውስጥ ያለአገልግሎት ከ4 ዓመት በላይ ተቀምጦ መገኘቱ፡፡

34.3 በክልሉ በተለያዩ ዞኖች የጤና ተቋማት ግንባታ የዘመኑን የህክመና መሳሪያዎች ስፋትና የአቀማመጥ ሁኔታ ሳያገናዝብ ስለሚገነቡ በ2007 ዓ.ም 27 አዳዲስ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ተገንብተው ራጅ /X-ray machine/፣ አጠባ ማሽን /loundery machine/ እና የህክምና መሳሪያዎች መቀቀያ/ማሙከኪያ/Autoclave machine/ለመትከል የኤሌክትሪክ ተሸካሚ ገመድ/cable/ ማሽኖችን ማንቀሳቀስ የማይችልና የግንባታው በሮች ማሽኖችን ማስገባት ባለመቻላቸው ገመዱ እንዲቀየርና በሮች ፈርሰው እንደገና እንዲሰሩ በመደረጉ ለ22 ሆስፒታሎች ተጨማሪ ውል በመያዝ ብር 27,585,432.05 እና 5 ሆስፒታሎች የወጣውን ተጨማሪ ወጪ መጠን ማወቅ ባይቻልም ከዋናው የግንባታ ውል ጋር የለውጥ ስራ /Varation work/ ተብለው የተሰሩ በመሆናቸው መንግስት ላልተገባ ተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግና መሳሪያዎችም ከአንድ አመት በላይ ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡

**አዴት የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል**

34.4 በ2009 በጀት ዓመት አንድ በብር 1,253,880.81 የተገዛ የአጠባ ማሽን /laundary machine/ የሚቀመጥበት /የተተከለበት/ የግንባታ ቦታ በትክክል ባለመሰራቱ አገልግሎት እየሰጠ ባለመሆኑ የኦፕሬሽንም ሆነ የተለያዩ ልብሶች በእጅ እየታጠቡ አገልግሎት እየሰጡ መገኘቱ፡፡

**ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል**

34.5 በሆስፒታሉ ውስጥ ደብሊው ኤም ጅ (WMG) ከሚባል ድርጅት የተገዛው 300 ሊትር የሚይዝ አውቶክላቭ /Autoclave/ የውሃ ማጣሪያ /Water distillation/ የሌለው በመሆኑ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ፡፡

34.6 በሆስፒታሉ ላቡራቶሪ ክፍል ውስጥ በሰውነት ውስጥ ያለውን ንጥረ ነገር ለመመርመር የሚያገለግሉ ሁለት ኤልክትሮ ላይት የህክምና መሳሪያ ሪኤጀንት ባለመኖሩ ያለ አገልግሎት ለ2 ዓመት ያህል መቀመጣቸው፡፡

34.7 በሆስፒታሉ በቀን 09/08/2007 ዓ.ም ገቢ የተደረገ ተንቀሳቀሽ የራጅ መሳሪያ /digital mobile X-ray machine/ዋጋው ብር 3,291,081.85 ሲሆን መሳሪያው ሲመጣ የጨረር መከላከያ አብሮ ስላልመጣለትና ፕሪነተሩ ከመሳሪያው ስላልተገጠመ አገልግሎት ሳይሰጥ ከ3 ዓመት በላይ ተቀምጦ መገኘቱ፡፡

**ደቡብ ወሎ ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ**

34.8 በዞኑ ጤና ጥበቃ መምሪያ ውስጥ ከመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ የተገዙ ሦስት SDD ፍሪጅ ሲቀርቡ የተሟላ መለዋወጫ አብሮ ባለመቅረቡ ተገዝተው ከመጡበት ከመስከረም 2008 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት ከ2 ዓመት በላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

34.9 በደሴ ዙሪያ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ለህክምና መሳሪያዎች ግዥ ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ (ግንባታ፣ የሰው ሃይልና መብራት) መሟላቱ የማይታይበት መሆኑ፡ ለምሳሌ በአብዛኛው የጤና ተቋማት በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የህክምና መሳሪያ እያላቸው መብራት የሌላቸው መሆኑ፡፡

**የደብረ ብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል**

34.10 በሆስፒታሉ የሚገዙ የህክምና መሳሪያዎች ዝርዝር መገለጫ /specification/ ሲዘጋጅ መሳሪያዎቹን እውቅና ባለው ባለሙያ የማይዘጋጅ መሆኑ፣የመብራት ችግር፣ የቦታ ጥበትና ግንባታ ችግር ስላለ የህክምና መሳሪያ ላይ የጥራት መጓደልና መበላሸት እንዲሁም ለህክምና መሳሪያዎች ግዥ ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊው ቅድመ ሁኔታ (ግንባታ፣የሰው ሃይልና መብራት) የሚታይበት አሰራር አለመኖር፡፡ /ለምሳሌ የቦታ ጥበት መኖርና የባለሙያ በገበያ ላይ አለመኖር፡፡/

**35. የህክምና መሳሪያዎች፣ መድሃኒቶች፣ ኬሚካሎችና ሪኤጀንቶች በወቅቱ ግዥ ተከናውኖላቸው እስከ ቦታው በመድረስ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ**

**35.1 በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ** የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎችን ለመግዛት ለኢትዮጵያ መድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ የውሉን 60% ቅድሚያ ክፍያ በቀን 06/09/2004 ዓ.ም. ብር 26,014,034.72፣በቀን 29/10/204 ብር 2,106,200.00፣ በቀን 30/09/2005 ብር 100,000,000.00፣ በቀን 27/09/2007 ብር 154,852,933.40፣በቀን 28/10/2008 ብር 100,000,000.00 እና በቀን 30/10/2009 ብር 15,061,180.52 በድምሩ ብር **398,034,348.64** በመክፈል ውል ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ከ4-6 ባሉት

ወራት ውስጥ የህክምና መሳሪያዎች እንዲቀርቡለት ውል ቢይዝም ከተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ውስጥ ብር 162,628,957.76 /41%/ የሚያወጡ መሳሪያዎችን ብቻ የቀረቡ ሲሆን ለቀሪው ብር **235,405,390.88 /59%/** ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎ በውሉ መሰረት የህክምና መሳሪያዎች እስከ 5 ዓመት በላይ ከኤጀንሲው አለመቅረባቸው፡፡

**35.2 በደቡብ ወሎ ዞን** የወሎ ዩኒቨርሲቲ ለደሴ ሪፈራል ሆስፒታል የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ለመግዛት ለኢትዮጵያ መድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ቅድሚያ ክፍያ 60% ብር 24,000,000.00 ተከፍሎ የህክምና መሳሪያዎች ከ4-6 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲቀርቡ ሃምሌ 2008 ዓ.ም ውል ቢያዝም የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት 08/06/2010 ዓ.ም ድረስ አለመቅረባቸው፡፡

**35.3** የደቡብ ወሎ ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ ከኢትዮጵያ መድሃኒት ፈንድ አቅርቦት የሚገዙ መድሃኒቶችን ኤጀንሲው በገባው ውለታ መሰረት በየጤና ተቋማቱ ማድረስ ሲገባው ከወረዳ ጽ/ቤቶች የሚያራግፋቸው በመሆኑ ጤና ተቋማቱ ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ መሆኑ፡፡ /ለአብነት ለጋንቦና ተንታ ወረዳ፡፡/

**36. በተለያዩ አካላት የጥራት ችግር ኖሮባቸው እንዲሰበሰቡ የታዘዙ መድሃኒቶች ክትትል መደረጉን በተመለከተ፤**

36.1 በጤና ጥበቃ ቢሮ የጥራት ችግር ያለባቸው መድሃኒቶች በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር በጥራት ችግር እንዲሰበሰቡ የታዘዙ መድሃኒቶች ለየዞኖች እንዲሰበሰቡ ደብዳቤ ከመጻፍ ባለፈ ምን ያህል መድሃኒት ተሰራጨ ምን ያህል ተሰበሰበ በሚል መረጃ በመያዝ የክትትልና ቁጥጥር ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፡፡

**36.2** በእርዳታም ይሁን በግዥ የሚቀርቡ የህክምና መሳሪያዎች የሚቀርቡት በመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በኩል ሲመጡ ስለመስራታቸውና አለመስራታቸው በባለሙያ ሳይረጋገጥ መራገፋቸው፡፡ **ለምሳሌ** ለፈለገ-ህይወት ሆስፒታል ከአሜሪካ በእርዳታ የተላኩት ከብር 20 ሚሊዮን በላይ የሚያወጡ የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ስለመስራታቸው ሲረጋገጡ አንድም የሚሰራ የህክምና መሣሪያ አለመገኘቱ፡፡

36.3 በደሴ ሪፈራል ሆስፒታል በፕሮግራም የቀረበ CD3.4,45,trit truce የተባለ ሪኤጀንት 99 ኪት ነጠላ ዋጋ ብር 7,387.44 ጠቅላላ ዋጋ ብር 731,356.60 ሲገባ የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ የሽረት ጊዜው ማለፉ፡፡

36.4 በደቡብ ወሎ ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ መድሃኒትም ይሁን የህክምና መገልገያ መሳሪዎች ወደ ጤና ተቋማት ሲገቡ ደህንነታቸው እየተፈተሸ ገቢ መደረግ ሲገባቸው በተንታ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በ2008 በጀት ዓመት የሽረት ጊዜ ያለፈባቸው 56 አይነት መድሃኒቶች ገቢ ተደርገው መገኘታቸው፡፡

**የደብረ ብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል**

36.5 በግዥም ይሁን በእርዳታ በመድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በኩል የሚቀርቡ የህክምና መሳሪያዎች ጥራትና ደህንነት በሆስፒታሉ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ባለሙያዎች የሚፈተሹበት አሰራር የለም፡፡ ለአብነትም ለህፃናት ህክምና ክፍል መድሀኒት ፈንድ ካስገባቸው አምስት የህጻናት ማሞቂያ /Incuvetor/ ውስጥ የአንዱ ዋጋ ብር 137,986.76 (በድምሩ ብር 689,933.80) የሚያወጣ አራቱ ወጥተው ወደ ስራ

ሲገቡ አንዱ 2 ወር እንደሰራ የተበላሸ መሆኑና አንደኛው ወጪ ተደርጎ ጥቅም ላይ ለማዋል ሲሞከር የማይሰራ መሆኑ፡፡

36.6 በክልሉም ሆነ በዞን ደረጃ የመድሀኒትን ጥራት ባይን ከማየት ያለፈ በባለሙያ የጥራት ቁጥጥር አይደረግም፤ በዚህም ምክንያት የጥራት ችግር ያለባቸው መድሃኒቶች የሚቀርቡበት ጊዜ አለ፤ ለአብነትም በመድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ (PFSA) የቀረበ ጉሉኮስ በብዛት እና በአይነት ስንት እንደሆነና መቸ እንደቀረበ መረጃ መቅረብ ባይችልም በአይን ሲታይ ቀለሙ የቀየረ በመሆኑ እንዲመለስ ተደርጎ መድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በናሙና መርምሮ በመረጋገጡ እንዲሰበሰብ የተደረገበት ጊዜ መኖሩ፡

36.7 ከመድሀኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በግዥም ሆነ በእርዳታ የሚመጡ መሳሪያዎች በሹፌር ስለሚላኩ እያንዳንዱ እቃ ዝርዝር አብሮ ስለማይላክ ርክክብ ለማድረግ ስለሚያስቸግር የሚመለከታቸውን አካላት በስልክ ሲጠየቁ ዘርዝራችሁ ተረከቡ ሰለሚባል የመጡትን ዘርዝሮ ከመረከብ ውጭ የትኛው መሳሪያና አክሰሰሪ አብሮ እንደተላከ ማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡ እንዲሁም መሳሪያዎች እንዴት መያዝ እንዳለባቸው በአቀማመጥና በማውረድ ላይ ስለሚፈጠረው ችግር የባለሙያ ጥንቃቄ የማይደረግ መሆኑ፣

36.8 ህዳር 20/2009 ዓ.ም በብር 1,517,607.00 የተገዛ አዲስ አውቶክሌብ ተከላ ተከናውኖለት ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ የቆመ በመሆኑ ሆስፒታሉ ርክክብ አልፈፀምም በማለቱ እስከ 20/02/2010 ዓ.ም ድረስ ቆሞ የሚገኝ፤ ሁለተኛው አውቶክሌብ ቢያንስ 10 ዓመት ማገልገል ያለበት ቢሆንም 1.2 ሚሊዮን ብር የተገዛ አንድ አመት እንዳገለገለ የተበላሸና መለዋወጫዎቹ ባለመቅረባቸው ሁለቱም አውቶክሌቦች ያለገልግሎት ስለተቀመጡ ሆስፒታሉ 20 ዓመት ባገለገለ ማንዋል አውቶክሌቭ በመጠቀሙ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ሰፊ ተፅኖ እያሳደረ መሆኑ፡፡

36.9 ሰኔ 2009 ዓ.ም የተገዛው ኬሚስትሪ አናላይዘር ጋር አብሮ ገቢ የተደረገው ኃይል ቆጣቢ (ups power saver) ሁለት ወር ሳይሰራ የተበላሸ፣ ሁለተኛው ሆስፒታሉ ከ2009 በፊት የገዛው አንድ ወር ሳይሰራ በመበላሸቱ አሁን ሁሉም መሳሪያዎች ምንም የሌላቸው ስለሆነ የመጣውን ናሙና እንደያዘ መብራት ሲሄድ መሳሪያው ለብልሽት እንዲዳረግ ከማድረጉ በተጨማሪ ውጤቱ ላይም ችግር እየፈጠረ መሆኑ፡፡

36.10 ለኦፐሬሽን የሚያገለግል ክር በፊት ስዊዘርላንድ (chromic catgut 2round) በብር 38.08 ይገዛ እንደነበርና ከቻይናና ከህንድ (chromic catgut 0 round) በብር 17.32 ተገዝቶ የሚመጣው በቀላሉ የሚበጠስ በመሆኑ ታካሚዎች ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑ፡፡

36.11 የደም መለኪያ (BP-apparatus) በመድሀኒት ፈንድ የቀረበው የጥራት ችግር የተስተዋለበት መሆኑ፡-

- ትክክለኛ ውጤት የማያሳይ ከመሆኑም በላይ አንዱ መሳሪያ ቢያንስ አንድ አመት ማገልገል የሚችል ቢሆንም ከሳምንት እስከ አንድ ወር ስለሚበላሽ ችግሩን ለመቅረፍ ሆስፒታሉ ሰኔ ወር 2009 የተገዛውን የእናቶች ክፍል ሀላፊ 3 ያንዱ ዋጋ ብር 1,150.00 ጠቅላላ ዋጋ ብር 3,450. በ2/12/2009 ወጭ ቢያደርግም በአንድ ሰው ላይ የተለያየ ውጤት በማሣየቱ ምክንያት በሰው ህይወት ላይ ችግር ስለሚፈጥር አገልግሎት እየተሰጠበት አለመሆኑ፡

37. ለህክምና መሳሪያዎች ብልሽት የተጠናከረ መረጃ በመያዝ በወቅቱ የመከላከልና የጥገና ስራ ስለመከናወኑ፤

**የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ**

37.1 በክልሉ ውስጥ የህክምና መሳሪያዎች ሲበላሹ ፈጥኖ የጥገና ስራ እየተሰራ አለመሆኑ፡፡ ለአብነትም የደባርቅ ሆስፒታል ራጅ /X-ray machine/ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እንዲጠገን ወይም መጠገን ካልተቻለም ሌላ እንዲገዛ ቢጠየቅም እስካሁን ድረስ መፍትሄ ያልተሰጠው መሆኑ፡፡

37.2 በምዕራብ አማራ የተለያዩ የጤና ተቋማት ውስጥ ያሉ ሄማቶሎጅ /Hematology/ የህክምና መሳሪያ (CBC Machine) በተለያዩ ጤና ጣቢያወች በ2007፣2008 እና 2009 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፡፡

*ማለትም ቻግኒ ጤና ጣቢያ ከ28/10/2008 ዓ.ም ጀምሮ፣ የዳንግላ ጤና ጣቢያ የተበላሸበት ጊዜው የማይታወቅ፣ ፈረስ ቤት ጤና ጣቢያ መስከረም 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ደጀን ጤና ጣቢያ መስከረም 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ደብረ-አሊያስ ጤና ጣቢያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ፣ ሞጣ ሆስፒታል ግንቦት 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ደ/ማርቆስ ሆስፒታል 2007 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቁይ ጤና ጣቢያ 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ነፋስ መውጫ ጤና ጣቢያ የካቲት 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ እስቴ ጤና ጣቢያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ፣ ወረታ ጤና ጣቢያ 2006 ዓ.ም ጀምሮ፣ አዲስ ዘመን ጤና ጣቢያ 13/09/2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ደባርቅ ሆስፒታል ግንቦት 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ መተማ ሆስፒታል የካቲት 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ሳንጃ ጤና ጣቢያ መስከረም 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ማክሰኝት ጤና ጣቢያ መስከረም 2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ አይከል ጤና ጣቢያ 06/07/2009 ዓ.ም ጀምሮ፣ ቆላድባ ጤና ጣቢያ ጥር 2007 ዓ.ም ጀምሮ፣ ገለጎ ጤና ጣቢያ መጋቢት 2008 ዓ.ም ጀምሮ ፣ አድርቃይ ጤና ጣቢያ መጋቢት 2009 ዓ.ም ጀምሮ እና ጓሃላ ጤና ጣቢያ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፡፡*

**የደሴ ሪፈራል ሆስፒታል**

37.3 በደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ውስጥ የሚገኙ የህክምና መሳሪዎችና ሁለት የልብስ ማጠቢያ መሳሪያ /Loundary machine/ ተበላሽተው አገልግሎት ሳይሰጡ ለብዙ ጊዜ ተቀምጠው የተገኙ ሲሆን አንዱ የልብስ ማጠቢያ መሳሪያ /Loundary machine/ ከ2004 ዓ.ም በፊት የተበላሸ መሆኑና አንዱ የልብስ ማጠቢያ መሳሪያ /Loundary machine/ ከጥር 2009 ዓ.ም ጀምሮ የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት 08/06/2010 ዓ.ም ድረስ ተበላሽተው የሚገኙ መሆኑ፡፡

**የደሴ ከተማ አስተዳደር ጤና ጥበቃ መምሪያ**

37.4 በከተማ አስተዳደሩ የባዮ ሜዲካል ባለሙያ ባለመኖሩ በህክምና መሳሪያዎች የብልሽት ሁኔታ መረጃ በመያዝ ጥገና እና ቅድመ መከላከል ስራ አለመከናወኑ፡፡

37.5 በሰኞ ገበያ ጤና አጠባበቅ የህክምና መሳሪያዎችን የሚጠግን ባለሙያ ባለመኖሩ መሳሪያዎችን ለማስጠገን አስቸጋሪ መሆኑ፡፡ በዚህም ምክንያት 1 ማይክሮስኮፕ፣ 2 ሸከር ተበላሽቶ ተቀምጧል፡፡

37.6 በደሴ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የተበላሹ የህክምና መሳሪያዎችን የሚጠግን ባለሙያ ባለመኖሩ ሁለት አጉልቶ የሚያሳያ የህክምና መሳሪያ /Microscop/፣ ማቀዝቀዣ፣ሴንት ሪፍውጅ፣ በርካታ የደም ግፊት መለኪያ /BP Apparatus/ እና ማዋለጃ /vacum/ ያለአገልግሎት ተከማችተው መገኘታቸው፡፡

**የደብረብርሃን ሪፈራል ሆስፒታል**

37.7 በራዲዮሎጂ ክፍል የልብ ችግር መመርመሪያ መሳሪያ (ECG) ከቀን 17/05/09 ዓ.ም ጀምሮ ተበላሽቶ ባለመጠገኑ አገልግሎት ያቆመ መሆኑ፣

37.8 የህክምና መሳሪያዎች /ማሽኖች/ ሲበላሹ በአብዛኛው የሚጠገኑት በአቅራቢ ድርጅቶች በመሆኑ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ቋሚ የሆነ የጥገና ውል ባለመኖሩ ለረጅም ጊዜ ተበላሽተው የሚቆሙ በመሆኑ ህሙማን የሚፈለገውን ምርመራ ሊያገኙ አለመቻላቸውና ለሌላ እንዲተላለፉ/ሪፈር/ የሚደረጉ በመሆኑ ለተጨማሪ ወጪ እና እንግልት እየተጋለጡ መሆኑ፡፡ (ለአብነት፡-ላብራቶሪ ክፍል ላይ ኬሚስትሪና ሄማቶሎጂ ማሽን፤)

37.9 የህክምና መሳሪያዎች ስራ የጀመሩበት ጊዜ፣የሚገኙበት ክፍልና የብልሽት ምክንያት ወ.ዘ.ተ የህይወት ታሪካቸውን በሚያሳይና በተጠቃለለ መንገድ መረጃ የማይያዝ፣ የተሟላ የጥገና ስራ የማይከናዎን፣ ቅድመ መከላከል ስራ አለመሰራቱ፡፡

37.10 በድንገተኛ ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ጥገና ቢደረግባላቸውም ሊሰሩ ያልቻሉ የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች የኦዲት ስራው እስከ ተጠናቀቀበት 22/02/2010 ዓ.ም ድረስ የማይሰሩ መሳሪያዎች መኖራቸው፡፡

*\/እነርሱም፡- BP cutf የተበላሸበት ጊዜ ከቀን 21/04/09 ጀምሮ፣ O2 Gzge የተበላሸበት ጊዜ ከቀን 21/04/09 ጀምሮ፣Whil chair የተበላሸበት ጊዜ ከቀን 11/11/09 ጀምሮ፣Pt monitor የተበላሸበት ጊዜ ከቀን 07/10/09 ጀምሮና O2 ሲሊንደር ጫፉ የተበላሸበት ጊዜ ከቀን 05/01/09 ጀምሮ የኦዲት ስራው እስከ ተጠናቀቀበት 22/02/2010 ዓ.ም ድረስ የማይሰሩ መሳሪያዎች መኖራቸው፡፡*

## 38. መድሃኒቶች፣ የህክምና መሳሪያዎችና ኬሚካሎች ወደ ጤና ተቋማት ገቢ እንደተደረጉ አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፡፡

**የጤና ጥበቃ ቢሮ**

38.1 የህክምና መሳሪያዎች ተገዝተው ከመጡ በኋላ ሳይተከሉ /Install ሳይደረጉ/ አንድ አመትና ከዚያ በላይ ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፡፡

38.2 በመብራት ኃይል አለመመጣጠን ምክንያት በሞጣ ሆስፒታል፣ በፈረስ ቤት ሆስፒታል፣ ግምጃ ቤት ጤና አጠባበቅ ጣቢያና ደብረ ማርቆስ ቀበሌ 04 ጤና አጠባበቅ ጣቢያ በመብራት ኃይል የሚሰሩ የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ተከላ ተደርጎ ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

**አዴት የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል**

38.3 የብር 1,253,880.81 ዋጋ ያለው አንድ ላዉንደሪ ማሽን ተተክሎ ስራ የጀመረ ቢሆንም ማሽኑ የሚቀመጥበት የግንባታ ቦታ በትክክል ባለመስራቱ ከግንቦት ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት እየሰጠ ባለመሆኑ የኦፕሬሽንም ሆነ የተለያዩ ልብሶች በእጅ እየታጠቡ አገልግሎት እየሰጡ መገኘታቸው፡፡

**የደሴ ሪፈራል ሆስፒታል**

38.4 በደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ውስጥ ጤና ጥ/ቢሮ ከአፍሮ ጀርመን ያስመጣቸው የህክምና መሳሪያዎች ሪኤጀንት ስለሌላቸው ማሽኖች ሳይተከሉ ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡ እነርሱም፡-

- የኬሚስትሪ ማሽን /Chemistry analyzer/ ዋጋው ብር 267,525.00 ሲሆን ከቀን 30/10/2008 ዓ.ም ጀምሮ ኢንስቶል ሳይደረግ መገኘቱ፤
- ሄማቶሎጅ ማሽን /Hematology analyzer/ ዋጋው ብር 281,623.56 ሲሆን ከቀን 30/10/2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 2010 ዓ.ም ድረስ ኢንስቶል ሳይደረግ መገኘቱ፡፡

38.5 በ2007 ዓ.ም ከአሜሪካ በእርዳታ የመጡ ሁለት ለቀዶ ጥገና ክፍል የሚያገለግሉ አንስቲዥን ማሽን አዲስ እንደታሸጉ ከ3 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸውና 2 የህጻናት ማሞቂያ /incubator/ በተመሳሳይ ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

38.6 በሆስፒታሉ ውስጥ በተለያየ ጊዜ የገቡ በርካታ አዳዲስ የህክምና መሳሪያዎች ያለአገልግሎት ስቶር ክፍል ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ አንዳንዶችን ምን አይነት መሳሪያ፣ ተግባራቸው ምን እንደሆነና ማን እንዳመጣቸው የሆስፒታሉ የስቶር ባለሙያ የማያውቋቸው መሳሪያዎች ተገኝተዋል፡፡ /ለአብነትም የህክምና መሳሪያዎችን ለመቀቀል /ለማሙከክ የሚያገለግሉ 12 ትንንሽ ማሙከኪያዎች /Autoclave/፣12 ማዋለጃ አልጋ /Delivery bed/ና 5 ለማዋለጃ አገልግሎት የሚውል /senction machine/ ከ2008 ዓ.ም በፊት ገቢ የሆኑ ያለአገልግሎት ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

38.7 በደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ውስጥ በኢትዮጵያ መድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ በኩል የቀረበና በቀን 14/08/2007 ዓ.ም ገቢ የተደረገ አንድ የህክምና መሳሪያዎችን ለመቀቀል /ለማሙከክ/ የሚያገለግል የህክምና መሳሪያ /Autoclave Machine/ ዋጋው ብር 1,907,600.89 ሲሆን ከእሽግ ሳይፈታ ከእስቶር ውጭ ከ3 ዓመት በላይ ያላገልግሎት ተቀምጦ መገኘቱ፡፡

**የደቡብ ወሎ ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ**

38.8 ከመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ለኮምቦልቻ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ በብር 139,863.51 የተገዛ አንድ ማጠቢያ ማሽን ከመስከረም 2008 በፊት ተከላ ተደርጎለት የኦዲቱ ስራ እስከተጠናቀቀበት የካቲት 2010 ዓ.ም ድረስ መስራት ባለመቻሉ ያለአገልግሎት ተቀምጦ መገኘቱ፡፡

38.9 ከመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ ለወረኢሉ አንድ፣ ለመካነ-ሰላም አንድ ከመስከረም 2008 ዓ.ም በፊት የተገዙ ሁለት የአጠባ ማሽን ዋጋ ብር 279,727.02 ሳይተከሉ/Install ሳይደረጉ/ ያለአገልግሎት ከ2 ዓመት በላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡

**የደሴ ከተማ አስተዳደር ጤና ጥበቃ መምሪያ**

38.10 በገራዶ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ከ2007 ዓ.ም በፊት የገቡ 138 ዓይነት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የህክምና መሳሪያዎች ያለአገልግሎት አንድ ክፍል ውስጥ ከ3 ዓመት በላይ ታሽገው መገኘታቸው፡፡

38.11 በሰኞ ገበያ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ በርካታ የህክምና መሳሪያዎች ሁለት ክፍል ውስጥ ተከማችተው መገኘታቸው፡፡

38.12 የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ጤና ተቋማት ላይ ተገዝተው ከገቡ በሁዋላ ያለአገልግሎት 5 አመትና ከዚያ በላይ ተቀምጠው መገኘታቸው። /ለአብነት ሲያደብርና ዋዩ ወረዳ ደነባ ጤና ጣቢያ/

38.13 መንዝ ቀያ ወረዳ ዘመሮ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የላብራቶሪ ክፍል መሳሪያዎች (ኬሚስትሪ ማሽንና ማቶሎጂ ማሽን) ለብዙ ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡና ለነዚህ ማሽኖች አገልግሎት የሚውሉ ሪኤጀንቶች ምንም ጥቅም ሳይሰጡ ተበላሽተው የተገኙ መሆኑ ተረጋግጧል።

- *አንኳለሳና ጠራ ወረዳ ጠንገን ጤና ጣቢያ በመብራት የሚንቀሳቀሱ የህክምና መሳሪያዎች (3ት አውቶክሌቭ፣4 ፍሪጅ ከሚያዝያ 2008 ዓ.ም ጀምሮ መብራት በመቋረጡ መሳሪያዎች ያለስራ መቀመጣቸው። በዚሁ ጤና ጣቢያ የላብራቶሪ ባለሙያ ባለመኖሩ ከሰኔ 2009 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት መሳሪያዎች አገልግሎት እየተሰጠ አይደለም።*

**የማጠቃለያ አስተያየት፡-**

የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና ተገቢ የሆነ የአፈፃፀም መርሃ ግብር በማዘጋጀት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰዱ፣ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ግኝቶች አንጻር በሌሎች አካባቢዎችም ያለውን ሁኔታ በዝርዝር በመገምገም የአፈጻጸም ብቃትን እና የአሠራር ስርዓትን ማሻሻል ብሎም በቀጣይ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች እንደ መነሻ በመወሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው በየሪፖርቶቻችን በዝርዝር አሳስበናል።

ስለሆነም በኦዲቱ የተመለከቱትን ግኝቶችና የአሰራር ክፍተቶች በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ኦዲቱ እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሚመለከታቸው አካላትና በም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ክትትል እንዲደረግባቸው እያሳሰብኩ የተከበሩ አፈ-ጉባዔ፣ የም/ቤት አባላት፣ የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በስራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም የመ/ቤታችን የስራ ሃላፊዎች፣ ይህን የኦዲት ስራ ለመስራት ከቤተሰቦቻቸው እና ከየመኖሪያቸው ቤታቸው ርቀው በመሄድ እና የሚገጥሟቸውን ችግሮች በመቋቋም ይህን ስራ ለዚህ ያበቁትን ኦዲተሮች እንዲሁም መላው የመቤቱ ሰራተኞች በዚህ ሪፖርት ለተመላከቱ የስራ ውጤቶች ላደረጋችሁት ጥረት በራሴና በመ/ቤቴ ስም ምስጋናየን እያቀረብኩ ሪፖርቱን በዚህ አጠናቅቃለሁ።

**"አመሰግናለሁ"**

**ገረመው ወርቁ /ረ/ፕሮፌሰር/**
**ዋና ኦዲተር**
**ባህር ዳር**